

ዋጋ ፩ ብር

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

# ትንሣኤ



በአ - ወልድ ስአላ - የታነፀው የቶማ ፋሲለደስ ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር ፲፫

ሰኔ ፲፱፻፸፫

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »


አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤
ም ክንፈ ርግብ ማርቆስ


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


# ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ደብዳቤዎች ............ ፩
ከድንኳን ወደ ቤተ ክርስቲያን ............ ፪
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን.... ፫
ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ የአብያተ ክርስቲያናትን መሪዎች ተቀበሉ.... ፭
ቅዱስ ሚካኤል ............ ፯
የዕንለ ማውታ ተስፋ ............ ፱
ዜና ሊቃውንት ............ ፲፩
የአፎምያ መፈተን ............ ፲፫
ቆማ ፋሲለደስ ............ ፲፭
የክርስቶስን ዕርገት ያየ ማን ነው ? ............ ፲፮
ርደተ መንፈስ ቅዱስ ............ ፲፯
አቡነ ዓቢየ እግዚእ ............ ፲፰
ጥንታውያን ሴቶችና ባህላቸው ............ ፳
ዝናምለዘር ............ ፳፩
ዜና ዕረፍት ............ ፳፪
ሰው በአግባቡ ቢሠራበት ሕግ መልካም ነው ............ ፳፫


ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፤

ከሁሉ አስቀድሜ ሰላምታ አቀርባለሁ መንፈሳዊ ሥራችሁም የተቃናና ለቤተ ክርስቲያናችንም ማጠንከሪያና ማስፋፊያ እንዲሆን ከልብ እየተመኘሁ የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች አቀርባለሁ ።

፩ኛ አንድ በእስልምና ሃይማኖት ያለ ሰው ክርስቲያኗን ሴት ለማግባት ቢፈልግና ቢያገባት ሴትዮዋም የስልምና ሃይማኖትን ብትቀበል ነገር ግን አብረው በባልና ሚስት ለብዙ ዘመን ከኖሩ በኋላ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ለመመለስ ቢፈልጉ ሁለቱም መጠመቅ ይባቸዋልን ?

፪ኛ/ ከጥምቀትና ከእምነት መቅደም የሚገባ የትኛው ነው ?

፫ኛ/ በንስሐ የማይሠረይ ኃጢአት የለም ይባላል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ኃጢአቱ አይሠረይለትም ይላል ይህ ስላል ገባኝ እንዲብራራልኝ እጠይቃለሁ ።

፬ኛ/ እግዚአብሔር አምላካችን ሁለተኛ የሚመጣበት ዕለትና ሰዓት አይታታወቅም ይላል ቅዱስ መጽሐፍ መተርጉማነ መጻሕፍት ሊቃውንት ሲያብራሩ ደግሞ በዘመነ ዮሐንስ በወርኃ መጋቢት በዕለተ እሁድ በመንፈቀ ሌሊት ይመጣል ይላሉ ይህ አባባል እንዴት ነው?

፭ኛ/ ጹሙ የሚል ቃል የሚገኘው ከምን መጽሐፍ እንደሆነ መጽሐፉን ከእነምዕራፉ በትንሣኤ መጽሔት ገልጻችሁ ብትጽፉልኝ እኔም ሆንኩኝ ሌሎች ለመረዳት እንችላለን ።

፮ኛ/ መጽሐፍ ቅዱስ ከየት ተገኘ ? በስንት ዓ/ም ተጻፈ ? ጸሐፍቱስ

ዲ/ተሻለ ወዳጆ ቡታ ጅራ

መልስ ፡-

ዲያቆን ተሻለ ወዳጆ መጽሔታችንን ተመልክተህና ጥቅሙንም ተገንዝበህ ላቀረብክልን ሰላምታ እያመሰገን ላቀረብካቸው ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ።

በመሠረቱ የስልምና ሃይማኖት ያለው ሰው ክርስቲያናዊቱን ሴት እንዲያገባ በክርስትና ሕግ አይፈቅድለትም ነገር ግን ክርስቲያንና እስላም በአንድ ላይ ትዳር መሥርተው ለመኖር ሁለቱም ቢስማሙ እስላሙ ይጠመቃል እንጂ ሴቷ ሁለተኛ አትጠመቅም ጥምቀት እንዴት ናትና ኤፌ 4.5 ።

ቢሆንም መጽሐፈ ቄደር ተደግሞ እንድትረጭ ይደረጋል ። ሁለተኛም እንዳትመለስ ትምህርት ያስፈልጋታል

፪ኛ/ ከጥምቀትና ከእምነት የሚቀድመው እምነት ነው ያመነ የተጠመቀ ይድናል በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጥምቀት እምነትን አስቀድሞ አስተምሯልና ማር ፲፮.፲፮ ።

አንዳንድ ጥያቄዎች ወንዱ በ፵ ቀን ሴቷ በ፹ ቀን መጠመቃቸው የወንጌሉን ቃል እንደሚጻረር በማድረግ ይናገራሉ ። ነገር ግን ወንዱ በ፵ ቀን ሴቷ በ፹ ቀን መጠመቃቸው የወንጌሉን ቃል የሚቃወም አይደለም ቤተ ክርስቲያናችን ይህንን ሕግ ወስና የምትጠቀምበት ምክንያት በልብ ወለድ አይደለም ።

አባታችን አዳም በተፈጠረ በ፵ ቀኑ እናታችን ሔዋን በተፈጠረች በ፹ ቀንዋ ወደገነት መግባታቸውን ምክንያት በማድረግ ነው መ/ኩፋሌ ፬. ዘሌ ፲፪ በመመልከት በሰፊው ለመረዳት ይቻላል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ቤተ ክርስቲያናችን ሕፃናትን የምታጠምቅበት ጊዜ የክርስትና አባትና እናት የምትጠይቀው ሕፃናቱን የክርስትና እምነት እንዲያስተምሯቸው ለማድረግ ነው እነርሱም ሕፃናቱን የማስተማር ግዴታ ስላለባቸው ለትምህርት ሲደርሱ በመጀመሪያ የሚያስተምሯቸው ሃይማኖታቸውን ይሆናል ።

፫ኛ/ ማንኛውም ኃጢአት በንስሐ የሚደመሰስ የሚሠረይ መሆኑ አያጠራጥርም መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ግን ኃጢአቱ አይሠረይለትም ስላልከው በንስሐ የማይሠረይ ኃጢአት የለም እንጂ ሆኖ ወደ እሳት ሲገባ የማይጤስ ሰው ሆኖ በዓለም የሚኖር ሁሉ ይበድላል ኃጢአትም ይሠራል ነገር ግን ሰው የሚሠራው ኃጢአት አንድ ሊሆን አይችልም ። አንዱ ከባድ ሌላው ቀላል ሊሆን ይችላል የሚሰጠውም ቀኖና እንደ ሠራው ኃጢአት የተለየ ይሆናል እንጂ አንድ ዓይነት ሊሆን አይችልም ።

በቅዱስ ወንጌልም መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ኃጢአቱ አይሠረይለትም ብሎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ከቀኖና ቀኖናውን ከፍዳዳ ፍዳውን ማበላለጡ ነው እንጂ በንስሐ የማይሠረይ ኃጢአት አለ ማለቱ አይደለም ። ስለዚህ የመልሳችን ማጠቃለያ ማንኛውም ኃጢአት በንስሐ ይሠረያል የሚለው ስለሆነ የበደሉ ሁሉ በንስሐ ወደፈጣሪያቸው እንዲቀርቡ መንፈሳዊ መልእክታችንን እናስተላልፋለን ።

፬ኛ/ እግዚአብሔር አምላካችን ሁለተኛ የሚመጣበት ዕለቱ ወርሁ ሰዓቱ ተለይቶ ሊታወቅ አይችልም ይህንንም ዕለት ማለት የሚመጣበትን ቀን እንዲነግራቸው ደቀ መዛሙርቱ ቢጠይቁትያችን ሰዓት ፍጥረታትም ሆኑ መላእክት አያውቋትም ከአብ በስተቀር ብሏቸዋል መተርጉማነ መጻሕፍት በዕለተ እሁድ በመንፈቀ ሌሊት በመጋቢት ወር በዘመነ ዮሐንስ እንደሚመጣ ቢናገሩም ብዙ ዘመነ ዮሐንስ ብዙ ወርኃ መጋቢት ብዙ ዕለት እሁድ ስላለ ለይቶ ለማወቅ አይችልም ።

፭ኛ/ ጹሙ የሚለው ቃል ከየትኛው መጽሐፍ እንደሚገኝ ግለጹልኝ ስላልከው ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፵ ሌሊትና ፵ መዓልት ጾሞ በልዩ ልዩ መንገድ የተፈታተነውን ሰይጣንን ድል መንሣቱ የጾምን ጠቃሚነት የሚያስረዳ ነው ማቴ ፲.፩-፲፩ እንዲሁም ሁለተኛ ማስረጃ ጌታች

www.ethiopianorthodox.org

# ከድንኳን ወደ ቤተ ክርስቲያን

ነቢዩ ሙሴ ሕዝበ እሥራኤልን የሚመራበትን ሕግ ለማግኘት ሲል ወደ ደብረ ሲና ወጥቶ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ጾሞ ሲፈጽም እግዚአብሔር አምላክ ሕጉን በጽላት ጽፎ ሰጥቶታል ። ሙሴ አሠርቱ ቃላት የተጻፈበትን ጽላት ከተቀበለ በኋላ ይህንን የተቀበለውን ጽላት የሚያስቀምጥበትና አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጽምበት ድንኳን እንዲሠራ እግዚአብሔር አዝዞታል ። ነገር ግን እንዴት አድርጐ እንደሚሠራ ቢያሳየውም ድንኳኑን ለመሥራት አልቻለም ። የሚያደርገው መላ ቅጡ ጠፍቶት ሲጨነቅ ከወገኑ ባስልኤልና ኤልያብ የሚባሉ ጥበበኞች አሥነሣለትና እርሱ እያሳያቸው የጽላተ ሕጉ መቀመጫና የእግዚአብሔር ስም መመስገኛ የሆነችውን ድንኳን ሠርተው ፈጸሙ ።

የተሠራችውም ድንኳን ዙሪያዋን ክብ ሁና ሦስት ክፍሎች ነበሯት የመጀመሪያው ክፍል ሕዝቡ የሚጸልዩበት ፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ካህናቱ አገልግሎት የሚያቀርቡበት ነበር ። ሦስተኛው ክፍል ግን አሠርቱ ቃላት የተጻፈበት ጽላት የሚቀመጥበት ሲሆን ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ጊዜ ገብቶ በመጀመሪያ ስለራሱ ቀጥሎም ስለሕዝቡ መሥዋዕት የሚያቀርበው በዚህ ክፍል ነበር ።

ስለድንኳኒቱ አሠራርና በዚያውም ውስጥ ስለአለው ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ "ለፊተኛይቱ ድንኳን የአገልግሎት ሥርዓትና የዚህ ዓለም የሆነው መቅደስ ነበራት የመጀመሪያይቱ ድንኳን ተዘጋጅታ ነበርና ፣ በእርሷም ቅድስት በምትባለው ውስጥ መቅረዙና ጠረጴዛው የመሥዋዕቱም ኅብስት ነበረባት ከሁለተኛውም መጋረጃ ወዲያ ቅድስተ ቅዱሳን የምትባል ድንኳን ነበረች ። በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ ። ሁለተኛይቱም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት በእርሷም ውስጥ መና ያለበት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ በላይዋም ማስተሰሪያውን የሚጋርዱ የክበሩ ኪሩቤል ነበሩ ስለእነዚህም ስለእያንዳንዳቸው ልንናገር አሁን አንችልም ። ብሏል ዕብ ፱. ፩-፭ ።

ይህችም ድንኳን አገልግሎት እየተፈጸመባት ከሙሴ እስከ ዳዊት ዘመን ቆይታለች ። ዳዊት ኢያውሴዎንን (ጠላቶቹን) ድል አድርጐ ደብረ ጽዮን በተባለችው ቤተ መንግሥት ተቀምጦ ሳለ ነቢዩ ናታን ሊጠይቀው ቢሄድ አዝኖ ተክዞ አገኘው ምን ሁነህ አዝነሃል አለው ዳዊትም ምነው አላዝን እኔ በዋንዛ በዘግባ በተሠራ ቤት ተቀምጨ ታቦተ ጽዮን በድንኳን ትኖራለች አለው ነቢዩ ናታንም መልሶ ጠላት ነው ጠፍቶልሃል ለምን ቤተ መቅደስን አትሠራም ቢለው ይህ ያለ ፈቃደ እግዚአብሔር ሊፈጸም አይችልምና እርዳኝ ስላለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠየቅ ሁለቱም ሱባኤ ገቡ ፣ ለዳዊት የበለጠ የሥጋዌ ነገር ተገልጾለት ወረከብናሁ ውስተ አመ ገዳም ናሁ ሰማዕናሁ በኤፍራታ እነሆ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በጎል ተጥሎ በጨርቅ ተጠቅልሎ እንደ ሕፃናት ሲያለቅስ ሰማነው ብሎ ሲናገር የቤተ መቅደስ ሥራ ደግሞ ለነቢዩ ለናታን ተገልጾለታል ።

ይኸውም አንተ ቤተ መቅደስን በስሜ ለመሥራት አትችልም ከአብራክህ የወጣው ልጅህ ሰሎሞን ግን የእኔ ስም የሚመሰገንበት ቤተ መቅደስ ይሠራልኛል የሚል ነው ፣ ዳዊት ቤተ መቅደስን ለመሥራት የነበረው አሳብ በዚሁ አከተመና የዳዊት መዋዕለ ሕይወት አልፎ ሰሎሞን ተተካ ለሰሎሞን ቤተ መቅደስን እንዲሠራ እግዚአብሔር አምላክ ስለፈቀደለት ታላቁንና ዝነኛውን ቤተ መቅደስ ሠርቶ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው አገልግሎት ሁሉ በቤተ መቅደስ እንዲፈጸም አደረገ ።

ይህንንም ወንጌላዊው ሉቃስ ሲገልጽ "እንዳየው ምስል አድርጎ ይሠራት ዘንድ ሙሴን ተናግሮ እንዳዘዘው የምስክር ድንኳን ከአባቶቻችን ዘንድ በምድረ በዳ ነበረች አባቶቻችንም ደግሞ በተራ ተቀብለው እግዚአብሔር በፊታቸው ያወጣቸውን የአሕዛብን ሀገር በያዙት ጊዜ ከኢያሱ ጋር አገቡት እስከ ዳዊት ዘመንም ድረስ ኖረች እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አግኝቶ ለያዕቆብ አምላክ ማደሪያን ያገኝ ዘንድ ለመነ ነገር ግን ሰሎሞን ቤት ሠራለት ብሏል የሐ ሥራ ፯.፵፭-፵፯ ።

ጠቢቡ ሰሎሞን እግዚአብሔር ስለፈቀደለት ታላቁንና ዝነኛውን ቤተ መቅደስ በሃያ ዓመታት ሠርቶ ከፈጸመ በኋላ እግዚአብሔር ለሰሎሞን በራዕይ ተገልጦ እንዲህ አለው ጸሎትህን ሰምቻለሁ ይህንም ስፍራ



ለራሴ ለመሥዋዕት ቤት መርጫለሁ ዝናብ እንዳይወርድ ሰማያትን ብዘጋ ወይም ምድሪቱን ይበላ ዘንድ አንበጣን ባዝዘው ወይም በሕዝብ ላይ ቸነፈር ብሰድድ በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ ፊቴንም ሲፈልጉ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ አሁንም በዚህ ስፍራ ለሚጸለይ ጸሎት ዓይኖቼ ይገለጣሉ ጆሮቼም ያዳምጣሉ አሁንም ስሜ ለዘለዓለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለሁ ቀድሻለሁም ። ዓይኖቼና ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ ። "ብሉታል 2ኛ ዜና መዋዕል ፯.፲፪-፲፯ ።

ከዚያ ዘመን ጀምሮ በደብተራ ኦሪት የነበረው አሠርቱ ቃላት የተጻፈበት ታቦት ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ አገልግሎቱ ሁሉ በዚያው የሚፈጸም ሆኗል ። ይህ ቤተ መቅደስ ከሰሎሞን ዘመን ጀምሮ እስከ ሕንፀተ ቤተ ክርስቲያን ድረስ መሥዋዕተ ኦሪት ሲሠዋበት ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲፈጸምበት ኑሯል ።

ነገር ግን በዚያ ቤተ መቅደስ የሚቀርበው መሥዋዕት ፍጹም ድኅነትን ለማሠጠት የማይችል በመሆኑ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶና እንደ ሕፃናት ቀስ በቀስ አድጎ በሰላሳ ዘመኑ ተጠምቆ ሲያበቃ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ ፵ ሌሊትና ፵ መዓልት ጾሟል መዋዕለ ጾሙን ከፈጸመ በኋላ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስተምሮ የአዳምን ልጆች ከፍዳና ከመርገም ነፃ ለማውጣት ሲል በቀራንዮ አደባባይ ተሰቅሎ ሙቶ በሞቱ ሞትን ድል ነሥቶ በመነሣት አዳ ኘነቱንና ከሃሊነቱን ላልተረዱት አስረድቷል ።

በቀራንዮ የተሠዋው ሥጋው የፈሰሰው ደሙ ፍጹም ድኅነት የሚሠጥ በመሆኑ የቀደመውን የበግ የፍየልና የከርማ መሥዋዕት አሳልፎታል ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ለአማንያን መሠጠት የተጀመረው ከስቅለቱ ዋዜማ ጀምሮ ንም የተወሰነ ቦታ ስላልነበረው በሐዋርያት ላይ ከፍ ያለ ችግርን አስከትሎ ነበር ።

ጳውሎስና በርናባስ እያስተማሩ ብዙ ሰዎችን በክርስቶስ ስም አሳምነው አጠመቁ ነገር ግን የክርስቶስን ሥጋና ደም የሚያቀበሉበት ቤተ ክርስቲያን ባለመኖረ ከፍ ያለ ችግር ደረሰባቸው ይህንን ችግር ለማቃለል የሚቻለው ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ በዚያ መገልገል መሆኑን ተገንዝበው ይህንን ጉዳይ ወደጴጥሮስና ዮሐንስ ላኩ ።

ጴጥሮስና ዮሐንስም ችግሩ ሊወገድ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ተገንዝበው ሱባኤ ገብተው ወደ እግዚአብሔር ቢጸልዩ አንዱን ሱባኤ እንደፈጸሙ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾና ሐዋርያትን በደመና ጠቅሶ ፊልጵስዩስ ከምትባል ቦታ አደረሳቸው በዚያም ጳውሎስና በርናባስ ተገኝተዋል ። ክርስቶስም በዚህ ቦታ በድንግል ማርያም በእናቴ ስም ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ ፈቃዴ ነው ፣ ብሎ የቤተ መቅደሱን መሥሪያ ቦታ ለክቶ ሰጥቷቸው ወደሰማይ ዓርጓል ።

ሐዋርያትም የቤተ ክርስቲያኑን ሕንፃ መሥራት ጀምረዋል ፣ የቤተ ክርስቲያኑም ሕንፃ የተጀመረው በሦስት ደንጊያዎች ሲሆን ሕንፃው ተጀምሮ እስከሚፈጸም ድረስ በየዕለቱ ሕንፃው በገንዛ እጁ እያደገ ይገኝ ነበር ።

የቤተ ክርስቲያኑም ሕንፃ ሲፈጸም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያት ጋር ቀድሶ አቅርቧታቸዋል። አማንያኑ የክርስቶስን ሥጋና ደም የተቀበሉት ሰኔ ፳፩ ቀን ነው ። ይህም ታሪክ በዚሁ ዕለት በሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር ተጽፎ ይገኛል ።

ቤተ ክርስቲያን በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተመሠረተች ምሥጢረ ሥጋውና ደሙ የሚሠጥባት አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምባት ቤተ ንጽሕ ቤተ በረከት ስለሆነች በዚህች ቦታ እየተገኙ መጸለይና የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም መቀበል ድኅነተ ሥጋንና ድኅነተ ነፍስን ያስገኛል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን

በስመ አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፡ በከተማና በገጠር የምትኖሩ ምዕመናን ፤

የሀገርን አንድነት የወገንን ነፃነት ለመጠበቅ በመሐልና በጠረፍ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ።

በልዩ ልዩ ሕመም ምክንያት በየሆስፒታሉ የምትገኙ ሕሙማን ።

ዓለምን ሁሉ የሚያድን ዓለሙን ሁሉ የሚወድ የሰላም ባለቤት አምላካችን እግዚአብሔር እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ ።

"ይትባረክ እግዚአብሔር ዘሰመየ ሕማሞተ ወልዱ ክብረ ወስብሐተ" የባሕርይ ልጁን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማምና ሞት ፤ ለእኛ ክብርና ጌትነት አድርጐ የሰጠን ልዑል እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን" (ዮሐንስ አፈ ወርቅ ድርሳን ፱)

ሥጋዊ ሞት የኃጢአት ውጤት እንደ መሆኑ መጠን በፍጡራን ዘንድ ሲነገር ያስደነግጣል ። ያስፈራል ። በተለይም ሞተ ነፍስ ከእግዚአብሔር መንግሥት የሚለይ በመሆኑ እጅግ ያስጨንቃል ።

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማምና ሞት ግን በኃጢአት ምክንያት ሳይሆን ለሰው ልጆች የዘለዓለምን ሕይወት የሚያድል ስለሆነ ሕማሙ ፤ ሞቱ ፤ ትንሣኤው ሲነገር ለሚያምኑበት ሁሉ ክብርና ጌትነት ነው ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህን ሲያመለክት "ተሰቅለ ከመ ያጽድቀነ ወተንሥአ ከመ ያንሥአነ" እኛን ሊያከብረን ተሰቀለ ፤ ከሞትም ሊያስነሣን ተነሣ ይላል (ሮሜ. ፬.፳፬)

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ለሰው ልጆች ክብርና ደስታ መሆኑን ሐዋርያትና ሊቃውንት ብቻ ሳይሆኑ በዘመነ ኦሪት የነበሩ ነቢያትም በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾላቸው አምልተውና አስፍተው ተናግረዋል ።

ከእነሱም አንዱ ነቢዩ ዳዊት "ተፈሣሕነ ወተሐሠይነ በኩሉ መዋዕሊነ ወተፈሣሕነ ህየንተ መዋዕል ዘአሕመምከነ ወህየንተ ዓመት እንተ ርኢናሃ ለእኪት" ርደተ ገሃነም ፈርደህብን መከራ በተቀበልንበት ቀንና ክፉ ባየንባቸው ዘመኖች ፈንታ ልጅነትን አግኝተን ከሞት ቁራኝነት ተላቀን ባለ ዘመናችን ሁሉ ፈጽሞ ደስ አለን ሲል ተናግሮአል (መዝ. ፹፱.፲፭)

ምዕመናን ሥጋዊ ሞት ያለባቸው ቢሆንም ከሞት በኋላ የዘላለም ሕይወት አላቸው ። ይህም ሕይወት በክርስቶስ ቸርነት ለሰው ልጆች የተሰጠ ትልቅ ክብርና ጸጋ ነው ።

ራሱ ክርስቶስ "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ በሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ። ሕያው የሆነ ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም ብሎአል (ዮሐ. ፲፩-፳፭)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ከሞት በኋላ ስላለው ትንሣኤና ሕይወት "ክርስቶስ ከሞቱት ሰዎች ሁሉ አስቀድሞ ተነሥቶአል ። በመጀመሪያው ሰው አዳም ሞት ሆኖአልና ። በክርስቶስም ትንሣኤ ሙታን ሆነ ። በአዳም ሁላችን እንደምንሞት ፤ እንዲሁ በክርስቶስ ሁላችንም እንነሣለን በማለት አስተምሮአል ። (፩ኛ. ቆሮ. ፲፭-፳)

እንግዲህ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ያለ ጌታ የክብር ትንሣኤ ሰጥቶ ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዲያወርሰን በሃይማኖት በተስፋ በፍቅር ጸንተን እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል ።

ምዕመናን የክርስቶስ ወገኖች መሆናቸው የሚታወቀው እርስ በርሳቸው በሚያሳዩት ፍቅርና ሰላም ነው ። ሰላምና ፍቅርም የተገኘው በክርስቶስ ነው ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ቃለ ምዕዳን ሲሰጡ ።

ዛሬ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በምናከብርበት በዚህ ዕለት የምናሳስበው ፤ ሃይማኖታችን የጸና እንደመሆኑ መጠን በጎ ምግባርም ያልተለየው እንዲሆን ነው ።

ስለዚህ ለበጎ ምግባር እንትጋ ፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንጸፈ ደይን ወድቀው የነበሩ ነፍሳትን በዚህ ዕለት እንደጐበኛቸው ፤ እኛም በረሀብና በልዩ ልዩ ችግር ያሉ ወገኖቻችንን በርኅራኄ ልንጐበኛቸው ይገባል ። የተራበውን ፣ የተራቆተውን ወገናችንን ከጐበኘን አምላካዊ ትእዛዝ ይፈጸማል ።

. በሃይማኖት ፣ በፍቅር አንድ ሆነን በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን እንጸልይ ።
. በዓሉን የሰላም የደስታ በዓል ያድርግልን
. አገራችን ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ይባርክ
. ለዓለም ሁሉ ሰላምን ይስጥልን ።



# ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ የአብያተ ክርስቲያናትን መሪዎች ተቀበሉ



ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ የአብያተ ክርስቲ ያናትን መሪዎች በአሜሪካ ሲቀበሉ

ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ የካቲት 29 ቀን 1978 ዓ/ም እንደኒውዮርክ ሰዓት አቆጣጠር ከሰዓት በኋላ በ2 ሰዓት ከ፴ ደቂቃ ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት ጋር በመሆን በጆን ኤፍ ኬኔዲ ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ጣቢያ በመገኘት ተቀብለዋቸዋል ።

የአብያተ ክርስቲያናቱም መሪዎች ከኦርቶዶክስ ከካቶሊክና ከሉተራውያን የተውጣጡ ነበሩ እነርሱም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዘመድኩን ብዙወርቅ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ምክትል ጸሐፊ ናቸው ።

በነጋውም የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ/ም በኒውዮርክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሦስቱም አብያተ ክርስቲያናት ተወክለው የመጡት እንግዶች በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው የሥርዓተ ቅዳሴው ተካፋዮች በመሆን አስቀድሰዋል የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት በብፁዕ አቡነ ገሪማ መሪነት የተከናወነ ሲሆን ብፁዕነታቸው ከወንጌሉ ምንባብ በኋላ ጾምን በሚመለከት ረገድ በብዛት ለተገኙት ምእመናን ሰፋ ያለ የወንጌል ትምህርትን ሰጥተዋል ።

የቅዳሴው ሥርዓት እንደተፈጸመም ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ እንግዶች ስለመጡበት ጉዳይ ገለጻ ካደረጉ በኋላ እንግዶቹን አንድ በአንድ ከምእመናኑ ጋር አስተዋውቀዋል ቀጥለውም በአሁኑ ጊዜ በድርቅ የተጐዱትን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ለመረዳት እናት ቤተ ክርስቲያን የምታደርገው ከፍተኛ ጥረት የሚያሳዩበት ነው ። በተለይም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የቤተ ክህነት ሠራተኞች ሁሉ ድርቁ ባጠቃቸው ሀገሮች እየተገኙ የሚያደርጉት ርዳታና ማጽናናት ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ጥሩ ምሳሌ ሆኖአቸዋል ። እኛም በውጭ ሀገር የምንገኘው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን ዓቅም ቢያንሰንም ከእናት ቤተ ክርስቲያን ጐን መሰለፋችንን ለመግለጽ እንወዳለን ብለዋል ።

ቀጥሎም ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው ምእመናኑ ከዚህ ቀደም ሲል በሀገራችን ላይ ለደረሰው ከፍተኛ ችግር ስለአደረጉት ታላቅ ርዳታ ምስጋናቸውን አቅርበው ወደፊትም ከስድስት ሚሊዮን የማያንስ ሕዝብ አሁንም ርዳታ እንደሚያስፈልገው ሰፋ ያለ ገለጻ አድርገዋል ። በዚሁ ዕለት ከሰዓት በኋላ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ለእንግዶች ታላቅ የምሳ ግብዣ አድርገዋል ። በግብዣውም ላይ የቤተ ክርስቲያኑ የሥራ አመራር ጉባኤ አባላትና ምእመናን የተገኙ ሲሆኑ እንግዶቹም ስለተደረገላቸው ግብዣ ብፁዕ አቡነ ገሪማ ምስጋናቸውን አቅርበዋል። ከዚያም የቤተ ክርስቲያኑ የሥራ አመራር ጉባኤ ሊቀ መንበር ብራዘር ወ/ሐዋርያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተለይም በምዕራብ ሀገሮች ስለአደረገችው የወንጌል ተልዕኮ ምስጋናቸውን አቅርበዋል ።

ከዚያም ቀጥሎ በሀገራችን ላይ ስለደረሰው ችግር ሲናገሩ ምንጊዜም በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው ችግር ከአእምሮአቸውን ሊጠፋ የማይችልና በአእምሯችንም ሠሌዳ ላይ ተስሎ ዘወትር የሚታየን ነው ፣ ወደፊትም ቢሆን ርዳታችንን አናቋርጥም በማለት ለእንግዶቹ አስረድተዋል ከዚህ በኋላ የግብዣው ሥነ ሥርዓት በጸሎት ተፈጽሟል ።

የዜናው አቅራቢ
መ/ፀሐይ ብርሃኑ
አሜሪካ ኒው ዮርክ



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት

ሚካኤል ማለት ድንቅ (እፁብ) ነገር ማለት ነው ። መላእክት ከእግዚአብሔር ወደሰው ከሰው ወደ እግዚአብሔር ለምሕረት ፣ ለምስጋናና ለተለያዩ ተልዕኮዎች ሲፋጠኑ የሚኖሩ ሕልፈት ፣ መቀያየር ፣ በየጊዜው መሾም መሻር የሌለባቸው ለብዛታቸው መጠን ለአሉበት ቦታ ወሰን የሌለውና መጀመሪያ በተሰጣቸው ሕግና ስርዓት ጸንተው የሚኖሩ ረቂቃን ፍጥረታት ናቸው ።

እግዚአብሔር በመጀመሪያው ቀን መላእክትን ፈጥሮ በተሰወራቸው ጊዜ ሣጥናኤልን አለቃ አድርጎ አስቀምጦት ነበር ። እሱ ግን በመታበይ የፈጣሪውን ሥልጣን ሽቶ እኔ ፈጠርኋችሁ ስላለ እሱን ከመሰሉት ሠራዊቶች ጋር ወደቀ ። ከዚህም በኋላ ቅዱስ ሚካኤልን የመላእክት ሁሉ የበላይ አለቃ አድርጎ ሹሞታል" በሰማይ ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉት ዘንዶውም (ዲያብሎስ) ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውም ። ከዚያ ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘለትም ራዕ ፲፪ ቁ. ፯

ሌሎችም መላእክት ፈጣሪያቸውን እስከሚያረጋግጡ ድረስ በትዕግሥት በመጠባበቃቸው በተለያዩ ሥራዎች ተሾመዋል ። ከዚያሞ ጀምሮ እያንዳንዳቸው ሊቃነ መላእክት የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለአንዲት ሴኮንድ እንኳ ባለማቋረጥ ሲያከናውኑ ይኖራሉ ።

ቅዱስ ሚካኤል ለሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ሲለምንና ሲያማልድ የሚኖር መልአክ በመሆኑ የምህረት መልአክ ተብሏል ። ስለዚህም ብዙ ክርስቲያኖች በቅዱስ ሚካኤል ስም ማኅበር በማቋቋም በአንድነትና በወንድማማችነት ፍቅር ፣ በመተሳሰር እርስ በእርስ ከመረዳዳት አልፈው ፣ የተራበውን በማብላት ፣ የተጠማውን በማጠጣት ፣ የታረዘውን በማልበስ ፣ የተጣላውን በማስታረቅ እንግዳ በመቀበል ይኖራሉ ። ይህም ለማኅበራዊ ኑሮ መሠረት ከመሆኑም ሌላ ለሌሎችም ክርስቲያኖችም ጥሩ ትምህርት በመሆን በዓለመ ሥጋም ሆነ በዓለመ ነፍስ ከፍ ያለ ዋጋ የሚያሰጥ የቅዱስ ወንጌል ቃል ነው ።



ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት

ሰኔ ፲፪ ቀን በየዓመቱ ቤተ ክርስቲያናችን የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በታላቅ ድምቀት ስታከብር የምትኖርበት ምክንያት ፩/ የመላእክት ሁሉ አለቃ ሆኖ ከፈጣሪው ሹመት የተቀበለበት ዕለትን መታሰቢያ በማድረግ ሲሆን ፣ ፪/ ባሕራን የተባለውን ጉልማሳ ከሞት ያዳነበት ዕለት በመሆኑ ነው ።

የባሕራን ወላጆች እግዚአብሔርን የሚፈሩ ቅዱስ ሚካኤልን የሚያከብሩ ክርስቲያኖች ሲሆኑ ባሕራን ከመወለዱ በፊት አባቱ ለእናቱ የቅዱስ ሚካኤልን መታሰቢያ በየወሩ እንዳታቋርጥ ተናዞ እንደሞተ ታሪኩ ይናገራል ። ባሕራንም በተወለደ ጊዜ ቤቱ በብርሃን ተሞልቶ ሕፃኑ ሲያድግ በጐረቤታቸው የሚገኘውን ያንድ ባለፀጋ ሀብት እንደሚወርስ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መሆኑን መልአኩ ይናገራል ። ልጁም አድጎ ፲ ዓመት ሲሞላው እናቱ ተቸግራ ስለነበር ሀብታሙ ጐረቤቷ ይህን ልጅ ወስጀ እያበላሁ እያጠጣሁና እያለበስሁ ይላላከኝ ዘንድ ስጭኝ ይላታል እሷም ከችግሯ የተነሳ እሺ ብላ ትሰጠዋለች ። ሀብታሙም "ይወርሳል" የሚለውን ቃል ቀድሞ ሰምቶ ስለነበር ልጁን ወስዶ በሣጥን ቆልፎ ወደ ባሕር ይጥለዋል ሣጥኑም በባሕሩ ላይ እየተንሳፈፈ ብዙ አገር አቋርጦ ከሄደ በኋላ አንድ የበግ እረኛ አግኝቶት ቢከፍተው ያማረ ልጅ ሆኖ በማግኘቱ ደስ ብሎት ወደ ቤቱ ወስዶ ያስቀምጠዋል ።

ልጁም በዚያው ቤት እያገለገለ ሲኖር ፣ ወደባሕር የጣለው ሀብታም ለንግድ ወደዚያ አገር ሄዶ በእንግድነት ያድራል ። ልጁንም ባሕራን እያሉ ሲጠሩት በሰማ ጊዜ ለምን ባሕራን እንዳሉት ቢጠይቅ ከባሕር የተገኘ በመሆኑ "ባሕራን" አልነው በማለት ታሪኩን ይነግሩታል ሀብታሙም እሱ ጥሎት የነበረው መሆኑን ከተረዳ በኋላ ለቤቱ ጌታ ብዙ ገንዘብ በመስጠት ባሕራን ወደቤቱ ደብዳቤ እንዲያደርስለት ይለምነዋል ። ደብዳቤውም "ይህ ልጅ ቀድሞ ወደባህር ጥየው የነበረው ነውና እንደደረሰ ሰው ሳያይ ገድለህ እንድትቀብረው" የሚል ለቤቱ አዛዥ የተጻፈ ነበር ። ባሕራንም ይህን የሞቱን ደብዳቤ ይዞ ሲጓዝ በመንገድ ላይ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል መንገደኛ መስሎ በፈረስ ላይ ሆኖ ሰላምታ ይሰጥና ከየት መጣህ ? ወዴትስ ትሄዳለህ ? ምን ይዘሃል ? በማለት ከየጠቀው በኋላ ደብዳቤውን ተቀብሎ በትንፋሹ እፍ በማለት ለውጦ ማኅተሙ እንዳለ "ይህ ብላቴና እንደደረሰ በቤትም በውጭም ያለውን ሀብቴን አውርሳችሁ እንዲን ልጇን እንድትድሩለት" የሚል አድርጎ ሰጥቶታል ።

ባሕራንም ወደ ሀብታሙ ቤት እንደደረሰ ደብዳቤውን ሰጥቶ ይነበብና በትዕዛዙ መሠረት ውርሱ ተፈጽሞ ልጇቷንም ድረውለት ሲደሰቱ ይሰነብታሉ ። ሀብታሙም ከሄደበት አገር ተመልሶ ወደቤቱ አቅራቢያ ሲደርስ አንዱን አሽከሩን አግኝቶ "ይህ የምሰማው ውካታና ዘፈንምንድነው ?ብሎ ቢጠይቀው" ይህማ በደብዳቤህ ጽፈህ በማኅተምህ አረጋግጠህ ባዘዝከው መሠረት ሀብትህን ንብረትህን ለባሕራን አውርሰን ልጅህንም ድረንለት ዓርባ ቀን ሙሉ ዘመድ አዝማዱ ጐረቤቱ ሁሉ እየበላ እየጠጣ እየዘፈነና እየተደሰተ ነው" አለው በዚህ ጊዜ ከገዛ ፈረሱ ላይ በድንጋጤ ወድቆ እንደሞተና ባሕራንም ሀብቱን ወርሶ የቅዱስ ሚካኤልን መታሰቢያ እያደረገ በእምነቱ ጸንቶ እንደኖረ ድርሳኑ በሰፊው ያብራራል ።

ከዚህ ታሪክ ብዙ ትምህርት እናገኛለን መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ለወደዳቸውና እግዚአብሔርን ከልብ ለሚያምኑ ሁሉ ያደረገላቸው ተአምራት ተዘርዝረው አያልቁም ብዙዎቹም በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ተጽፈው ይገኛሉ ።

ለምሳሌ እሥራኤል ከግብፅ እንደወጡ በመንገድ ላይ እንዴት እንደረዳቸው ይስሐቅንም ለመሥዋዕትነት ከተቃጣበት ቢለዋ ድኖ በምትኩ የሚሠዋውን በግ እንዳመለከተ ፣ ሕዝቅያስን ከሰናክሬምና ሠራዊቱ እጅ እንዳዳነው ስንመለከት የባሕራንም ታሪክ ይህንን ይመስላል ።

ሀብታሙ ሰው በሀብቱና በጉልበቱ ተመክቶ ባሕራንን ወደባሕር ከጣለው በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነትና በመልአኩ ተራዳኢነት እንደዳነ ሲያይ ፣ በአድራጎቱ በመጸጸትና በመመለስ ፋንታ እንደገና ጠማረ ሞቱን (የሞቱን ደብዳቤ) አስይዞ በግፍ እንዲሞት ወደቤቱ በመላኩ ሀብቱንም ሕይወቱንም አጣ በመጀመሪያው ስሕተቱ በጸጸት ኖሮ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነውና ባልሞተም ነበር ። ይህን በመሰለ መንገድ ዛሬም በወንድሞቻቸው ላይ በተንኮልና በምቀኝነት ተነሳስተው ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ሌላውን ለማጥፋት ወይም ለማስጠፋት የሚሹ ቢኖሩ ይህ ታሪክ ጥሩ ትምህርት ሊሆናቸው ይገባል ።

በዕውቀት ሠርቶ ካገኙት ሀብት መብላት ፣ መጠጣት ፣ መልበስና ማጌጥ ከዚያም በታች ያለመጠን ያጡ ወንድሞችን መርዳት፣ለሥጋውያንም ሆነ ለመንፈሳውያን ድርጅቶችም የሚፈለገውን አስተዋጽኦ እየከፈሉ መኖር ለማናቸውም ሰው የተቀደሰ ተግባር መሆኑ የታወቀ ነው ። በዚህም ዓይነት የተገኘውን ሀብት እግዚአብሔር ይባርከዋል ።

ባለፀጋው ሰው በባሕራን ና በቤተሰቦቹ ኑሮና አምልኮተ እግዚአብሔር ሲዘብትባቸው እንደነበር ታሪኩ ይናገራል ። እውነተኞች ክርስቲያኖች ሀብታቸውን ላጣ በመርዳት ፣ ለተራበና ለተጠማም በመለገስ በመላእክትም ሆነ በሌሎች ቅዱሳን ስም መታሰቢያ በማድረግ ጨርሰው ቢደኸዩም የማያልፈውን ሀብት በማይጠፋ መዝገብ አስመዝግበዋል ። ነገር ግን ሀብታቸውን ተቆጣጥረው በቁም ነገር ላይ ማዋል የ ባለፀጐች ለስከር፡ለዝሙት፡ ለሌላም የተንኰል ተግባር የሚያውሉት ከሆነ የዚህ ሀብታም እድል እንደሚገጥማቸው ግልጽ ነው ።

ክርስቲያኖች ሀብታቸው እየበዛ በሄደ ቁጥር ከእግዚአብሔር ጋር ያለውም ግንኙነታቸው በዚያው ልክ እየጠነከረ ይሄዳል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "አንድ አገልጋይ ለሁለት ጌቶች መገዛት አይችልም" ሲል በወንጌል የተናገረው ስለዚህ ነው ። ይህንንም ስንል ገንዘብ አስፈላጊ አይደለም ማለታችን አይደለም ። በቅድሚያ ፕሮግራም አው





www.ethiopianorthodox.org

# የእጓለ ማውታ ተስፋ

ከሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገ/ ሥላሴ

ዓለማችን በችግር የተወጠረ ኅብረተሰብ ይበዛበታል ። የችግሩ መንስዔ በፖለቲካ ፣ በኤኮኖሚና በማኅበራዊ ሥርዓት ወደኋላ መቅረት ሲሆን የኅብረተሰቡ በችግር መጋለጥ ሌላ ምክንያት ደግሞ ጦርነት ፣ ስደት ፣ ድርቅ የሚያስከትለው ችግርና የመሳሰለው ሁሉ ነው ።

ጉዳቱ ከሚያጠቃቸው መካከል የመጀመሪያዎቹ ሕፃናት መሆናቸው አይካድም ፤ መውለድና መወለድ ብቻ አይበቃም እንደሚባለው ሕፃናት ከተወለዱና ወደዚህ ዓለም ከተገለጡ በኋላ በእንክብካቤ ማደግ ይገባቸዋል ። ነገር ግን ወላጆች ልጆችን ከወለዱ በኋላ በትክክል ለማሳደግ ባለመቻላቸው በሕፃናቱ ላይ መቆርቆዝ ፣ በቀ

ጥተን አስፈላጊ ለሆኑ ቁም ነገሮች እናውለው ማለት ነው ።

ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ባሕራን -የተባለውን ብላቴና በመንገዱ ሁሉ እንዴት እንደረዳው ተመልክተናል ። እኛም እምነታችን የበረታ እግዚአብሔርን የምንፈራና በመልአኩም ስም መታሰቢያውን እያደረግን ከለመነው ይህን ከመሳሰለው አደጋ እንደምንድን አረጋግጦልናል ። በስሙ የሰጠ ፣ ድርሳኑን ያነበበ ፣ በቤቱም እንኳ ያስቀመጠ በራሱ በቤተሰቡ ፣ በእንስሳውና በንብረቱ ላይ ጥፋት አይመጣባትም ፤ ረሀብና በሽታም በቤቱ አይገባም የሚል በድርሳኑ ተጽፎ እናገኛለን ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ እንጂ እንዲሁ የተጻፈ አይደለም ። "ክፉ ነገር ወደአንተ አይቀርብም ፤ በመንገድህ ሁሉ ይጠብቅህ ዘንድ መላእክቱን ስላንተ ያዛቸዋልና እግርህንም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሱሀል" መዝ ፺ ቁ ፩-፲፪ ።

መ/ መንክር ዋሴ

ሳሉ በደዌ መለከፍና በመጨረሻም መሞት ይደርስባቸዋል ።

አሁን ዓለማችን ያለችበትንም ሁኔታ በትክክል ብንመለከት ችግር የተወጠረች ማኅበራዊ ሥርዓቷ የተዛባ ሆኖ እናገኛታለን ።

ሕፃናት በሰላም ጊዜ በሚደርስባቸው ሕመም እናቶቻቸውና አባቶቻቸው ይሞቱባቸውና ያላሳዳጊ ይቀራሉ ። "መውለድ ቀላል ነው ፣ ቁም ነገሩ ከማሳደጉ ላይ ነው" ተብሏል ።

ይህ እውነተኛና ተጨባጭ አባባል መሆኑን ሁሉም ያውቀዋል ። በጦርነት ጊዜ አባቶቻቸው በጦር ሜዳ ወድቀው ሲቀሩባቸው እናቶቻቸውም ከደረሰባቸው ብስጭትና ጉስቁልና የተነሳ ሲሞቱባቸው ሕፃናቱ ያለ አሳዳጊ በመቅረት ለታላቅ ፈተናና ችግር ይጋለጣሉ ።

ታድርና ሲነጋ ሥራ መሥራት ለእናቷም ሆነ ለታናናሾች ወንድሞቿ ለራሷም ምግብ ማግኘት ግዴታዋ ስለነበር በርትታ ትሠራ ነበር ይላል ታሪኳን የመዘገበው የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀግና ወጣቷ እናቷ ስትቸገር አይቼ ሰተት ብዬ ወደ ስሯ ገባሁ ፣ ተጋባንም የጓሮውንም አትክልት ዓላማ ጀመርን ፣ ከብቶችንም ማርባት ቀጠልኩ ።

ወንድሞቿም እየተማሩ ፣ ጎልማሶች ሆኑ ፣ ወንድ ልጅም ወለድን ፣ ልጁም አደገና ወደ ትምህርት ቤት እንደገባ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተጀመረ ። በአገርና በነፃነት ዋዛ የለምና ወደ ጦር ሜዳ ሄድኩ ይልና የዚያን ጊዜው ጀግናው እስክንድር ጦርነቱ ያስከተለውን ችግር እንዲህ ሲል ይገልጸዋል እኔም ወደ ጦር ሜዳ ስዘምት ባለቤቴ በፋብሪካ ውስጥ ትሠራ ነበር ።



ቅዱስነታቸው የዕጓለ ማውታ ሕፃናትን ሲጐበኙ

እንዲህ ያለው ችግር በዓለም የተፈጸመና በመፈጸምም ላይ ያለ መሆኑ ስውር አይደለም ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ አንዲት ሕፃን አባቷ ይሞትባታል ፣ እናቷ ያለአባት ስታሳድጋት በድንገት ትታመምባታለች ፤ ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በማጣት እናቷን ስታስታምም

ሁለት ወንድሞቿ ለእናት አገራቸው መሥዋዕት ለመሆንና ከጠላት ጋር ለመተናነቅ ዘምተዋል ፤ ሁለቱም ወንድሞቿ በጦር ሜዳ ሞቱ ፣ የእኔ ቤተሰቦች ጠላት ረበከተማችን በጣለው ቦምብ ተመትተው አለቁ ፤ በጦርነቱ ፍጻሜ አካባቢ ልጃችን ረሃብን ሊቋቋም ስላልቻለ ሞተ ። እኔ ከጦር ሜዳ ስመለስ ሚስ



ቴን ከሕያዋን በታች ከሙታን በላይ ሆና ፣ መልኳ ጠቁሮ ጠላሽት መስላ ፣ ተጎሳቁላ ከንፈሮቿ አርረውና ጠቁረው አገኘኋት ። እርሷ ናት ብዬ ማወቅና ማመን ተሳነኝይላል እስክንድር

ከደረሰባቸው አሀጉራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ሀገራችን ናት አገራችንን ድርቅ እየደጋገመ መትቷታል ፣ ብዙዎች ወላጆች ድርቅ በአስከተለው ችግር አልቀዋል ፣ ከሁሉ አስቀድሞ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት እናት አባታቸው የሞቱባቸውን ሕፃናት ሲጐበኙ ።

በዝክረ ታሪኩ ።

እንደገና አዲስ ኑሮ ጀመርን ፣ እኔ በመምህርነት ተቀጠርኩ መከራ የተፈራረቀባት ውዷ ባለቤቴ በአዳሪ ትምህርት ቤት መምህርት ሆነች ፣ ከዚያ በኋላ ልጅ አልወለድንም ። ነገር ግን ቤታችን እናቶቻቸውንና አባቶቻቸውን ባጡ "እጓለ ማውታ" የተሟላ ነበር ችግርን የሚያውቅ ችግርን የቀመሰ ነው ። እንደሚባለው ሁሉ እኔም ሆንኩ ባለቤቴ በአሰቃቂው ጦርነት ምክንያት ቤተሰቦቻችንን ልጆቻችንን ያጣን እንደመሆናችን መጠን "እጓለ ማውታን" እየተንከባከቡ ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘባችን ለእጓለ ማውታ እንክብካቤ ማድረግ ጀመርን ርኅሩኋ ባለቤቴ ትመግባቸው ፣ ጸጉራቸውንም ታስተካክላቸው ፣ ልብሳቸውንም ትጠቀቅም ነበር ። በትምህርታቸው እንዲበረቱ እናስጠናቸውና እንረዳቸው ነበር በማለት እስክንድር የተባለ ሰው የተረከውን ከአንድ የታሪክ መጽሐፍ አንብቤያለሁ ፤ በጦርነትም ሆነ ድርቅ ባስከተለው ችግር እናት አባቶቻቸውን ያጡ ሕፃናት ቁጥር እየበረከተ ሄዷል እንዲህ ዓይነቱ ችግር

ለችግርና ለሞት የተጋለጡት ሕፃናት በሺህ የሚቆጠሩ መሆናቸው ግልጽ ነው ።

ከሞት ለተረፉት "ለእጓለ ማውታ ተስፋ" ማን ነበር ? በመጀመሪያ ደረጃ አብዮታዊ መንግሥት ሲሆን ቀጥሎ አቅሟ በሚፈቅድላት መሠረት "የእጓለ ማውታ ተስፋ" የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲንንና የዓለም ኅብረተሰብ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በሚያደርግበት ጊዜ "ኢየኅድገክሙ እጓለ ማውታ ትኩኑ "የሙታን ልጆች እንደሆናችሁ አልተዋችሁም በማለት የተናገረውን አምላካዊ ቃል መመሪያ በማድረግ ሁልጊዜ የሙታን ልጆችንና ወልደው ማሳደግ የተሳናቸውን የድሆች ልጆችን እየሰበሰበች ስታሳድግ ኖራለች ። በአገራችን በደረሰው ድርቅና አድኃሪው የሶማሊያ ስርጎ ገብ ጦርነት ምክንያት እናቶቻቸውንና አባቶቻቸውን አጥተው ያለአሳዳጊ የቀሩትን ሕፃናት ከ1966 ጀምሮ በማሰባሰብ አዳሪ ትምህርት ቤት ከፍታ ምግብ ፣

ልብስ ፣ የትምህርት ቁሳቁስ እየገዛች በማሳደግና በማስተማር ላይ ትገኛለች ። በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባና በየክፍላተ ሀገሩ የምታሳድጋቸውና የምታስተምራቸው ሕፃናት ቁጥር ከ5600 በላይ ደርሷል ።

ይህም በድርቅ ምክንያት ከትዳራቸው የተፈናቀሉትን በየመመገቢያው ጣቢያዎች በወሎ ፣ በትግራይ ፣ በጐንደር ፣ በሸዋና በባሌ ክፍላተ ሀገር ከምትሰጠው አገልግሎት ሌላ ለሕፃናቱ ብቻ የምታበረክተው ሰብአዊና ፍጹም የሆነ የእናትነት እንክብካቤ ነው ።

ከ1966 ጀምሮ በምግብ በልብስ ፣ በትምህርት እየተንከባከበች ካሳደገቻቸው መካከልም ከዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ፈጽመው ሥራ የያዙ በውጭ ሀገር የነፃ ትምህርት ዕድል አግኝተው የሄዱ ፣ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ተቀጥረው የወር ደመወዝ እያገኙ የሚሠሩ በጠቅላላ ለኢትዮጵያ ኅብረተሰብ የጋራ ብልጽግና የሚታገሉ ብዙዎች ናቸው ።

በዚህም መልካም ውጤት ቤተ ክርስቲያናችን ደስታዋ ዕጥፍ ድርብ ነው ። ቤተ ክርስቲያናችን አንዱ ሌላው መኖር እንዳለበት የምታስተምር የርኅራኄ መዝገብ ናት እያንዳንዱ ኅብረተሰብ ፍቅር ካለውና ከተባበረ ይረዳዳል በአንድነቱና በፍቅሩ ችግርን ሊያሸንፍ ይችላል ።

እኒያ ከእናቶቻቸው ጡትና እንክብካቤ በሕፃንነታቸው የተነጠሉ ፣መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ያሳደጓቸውና የሚያሳድጓቸውን ሕፃናት በአካል ጎልምሰው በዕውቀት በልጽገው ፣ በሥራ ጠንክረው ኑሯቸውን መሥርተው ሲታዩ ከማየት የበለጠ ደስታ የለም ።

በአሁኑ ጊዜ ችግሩ ፈጽሞ ተወግዷል ፤ እጓለ ማውታ አሳዳጊ አግኝተዋል ማለት አይቻልም ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ችግር አለብን ። ይሁንና ችግሩን ተቋቁመን መልካም ውጤትን ማስገኘት የምንችለው ተባብረን ስንሠራና እርስ በርሳችን ስንረዳዳ ብቻ መሆኑን ከልብ ልንረዳ ይገባል ። "የእጓለ ማውታ"



www.ethiopianorthodox.org

# የአፎምያ መፈተን

የቅድስተ አፎምን ታሪክ ከመናገራ ችን በፊት የአንዳንድ ደጋግ ክርስቲያ ኖችን ፈተና መናገሩ የአፎምያን በሰይ ጣን መፈተን እሙን ያደርገዋል ።

ፈተና በልዩ ልዩ ምክንያት ሊመጣ የሚችል ሲሆን እኛ ግን በሁለት አቅ ጣጫ የሚመጣውን ፈተና ነው የምንና ገረው አንዱ በኃጢአት ምክንያት የሚ መጣ ፈተና ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሰዎች እራሳቸውን ለጾም ለጸሎት ለስግ ደት አስገዝተው በንስሐና በቀኖና በሚ ኖሩበት ጊዜ ሰይጣን በቀናኢነቱ የሚ

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቅብም በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው ። ከፈተና በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰ ጣቸውን የሕይወት አክሊል ይቀበላ ልና ሲል ተናግሩዋል ያዕቆብ ፩ ፡ ፲፪

በዚህ መሠረት በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ በእምነታቸው ጥንካሬና በመንፈሳዊነታቸው ተፈትነው በድል አድራጊነት ወጥተው በክብርና በቅድ ስና ያረፉ ብዙ ለዎች ናቸው ።

ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ኢዮብ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ኢዮብ ነው ። ኢዮብ በሰይጣን ፈታኝነት ከእግር እስከ ራሱ ድረስ በቁስል ተመቶ ቢሠቃይም የደረሰበትን ፈተና በትዕግሥት ድል በመንሳቱ የጽድቅ ባለ ሆኖ በክብር እንዳረፈ በመጽሐፈ ኢዮብ ተጽፎ ስለ ሚገኝ መጽሐፉን በጥሙና አንብቦ መረዳቱ እጅግ የተሻለ ነው ።

እንዲሁም አምላክ ሰላም ክርስቶስ ለክርስቲያኖች ሁሉ ምሳሌና አብነት ለመሆን በገዳመ ቆሮንቶስ በሰይጣን እንደተፈተነ ዲያብሎስን ድል እንደነ ሣው በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፏል ማቴ ፬ ፡ ፩ - ፲፩ በዚህ መነሻነት ለመግ ለጽ የፈለገው ስለቅድስት አፎምያ በሰይ ጣን መፈተን ነው የአፎምያ ባሏ አስተራ ኒቆስ ይባል ነበር በሞት ከእርሷ ከተለያ በኋላ ቃል ኪዳኗን በመጠበቅ ከዚያ በፊት ይዘክሩት የነበሩትን የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በየወሩ ከመዘከሯም ሌላ የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል አሰላ በመአልትም ሆነ በሌሊት በሥዕሉ ፊት ለፊት እየቆመች ወደእግዚአብሔር ትጸልይና ስትማጸን ነበር ይህንን የተቀ ደሰ ዓላማዋን ለማሰናከል ሰይጣን ይቀ ና ስለነበር በጎ ሥራዋን ለማስተው ይፈ ታተናት ጀመር ።

አፎምያም በእምነት የጸናች ለመን ፈሳዊ ስነ ምግባር እራሷን ያስገዛችና ፈራሂተ እግዚአብሔር ከመሆኗም ሌላ በተለይ የተራቡትን መመገብ ፡ የታ ረዙትን ማልበስ የታመሙትን መጠ የቅ ፤ ያዘኑትን ማጽናናት ፡ ተስፋ የቆ ረጡትንም ማረጋጋት የዘውትር ዓላ ማዋ ስለ ነበር ፀሐመዷ በነበረው ሕብ ረተሰብ ዘንድ ተወዳጅ የሆነች መን ፈሳዊ እናትብ ነበረች ለዚህም የተ የተቀደሰ ሥራ እንድትበቃ ያንሳሳት ተርቢ እብልታችሁኛልና ፡ ተጠምቼ

ወደ ገጽ ፲፱ የዞረ

ተስፋ” ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የ ውታንና የድሆችን ልጆች የምታሳድ ግበት የምግባረ ሠናይ መርሐ ግብር እጅግ ሰፊ ስለሆነ ምዕመናን በገንዘባ ቸው በጉልበታቸውና በመልካም አሳ ባቻው ሊረዱት ይገባል ።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ለሥራ ጉዳይ ወደ አውሮፓ ሄዶ በአረፈበት ሆቴል ማታ ቴሌቪዥን ከፍቶ ሳለ የኢትዮጵ የረኀብ ሰቀቀን የሚያሳይ ፊልም እንደ አጋጣሚ መመልከት ችሏል ። በፊልሙ ተቀርጾ የቀረበ አጭር ድራማ ነበር ። ሁለት ልጆች ያሉት አንድ ባለጸጋ ማታ በምቹ አልጋ ላይ ተገቶ ሳለ አንድ ሰው



ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው እናት አባታቸው የሞቱባቸውን እጓለማውታ ሲጉበኙ ።

በድንገት ይመጣና ልጆችህ ሞቱ በማ ረት ያረዳዋል ። ባለጸጋውም ደንግጦ ይጮኸ ስለገባ ልጆች ደንግጠው ከመ ኝታቸው ይነሳሉ ። ባለጸጋው ግራ ይገ ባውና በመርዶ አርጂው ላይ እንደመብ ረቅ ይጮኸበታል ።

ልጆቼ እነሆ በሕይወት አሉ ለምን በሐሰት አስደነገጥከኝ ቢለው “ልጆ ችህ እነዚህ ብቻ ናቸውን ? የዓለም ኅብ ረተሰብ ልጆችም እኮ ያንተ ልጆች ናቸው በኢትዮጵያ ኢትዮጵያውያን ልጆችህ በረሃብ እየሞቱ ናቸው ፤ በባ ንክ ካከማቸኸው ገንዘብ የተቻለህን ያህል ላክና ኢትዮጵያውያን ልጆችን አድናቸው በማለት ምክር ሰጠው ባለ ጸጋውም በሒሳቡ እንደተስማማ የድራ ማው ትርኢይት ተፈጸመ ።

በድራማው የታየው ቁም ነገር የተ መላበት ነው ። እያንዳንዱ ልጆቼ የሚላ ቸውና የሚንከባከባቸው ከአብራኩ ተከ ፍለው የተወለዱትን ልጆች ብቻ ላይ ሆን እናት አባት ያጡ እጓለ ማውታ የራሱ ልጆች መሆናቸውን በመገንዘብ ከመንግሥትና ከቤተ ክርስቲያናችን ጋር በመተባበር ማሳደግ ኃላፊነቱ መሆ ኑን መረዳት ይገባል ።



ከገጽ ፩ የዞረ

ን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ያስተ ምርበት በነበረው ወቅት የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደእርሱ ቀርበው እኛና ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ የምንጦመው የአንተ ደቀ መዛሙርት የማይጦሙት ለምንድን ነው ? ብለው ቢጠይቁት ጌታችን ሲመልስ ሚዜዎቹ ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ መጾም አይገባቸ ውም ። ሙሽራው ከእነርሱ ከተለየ በኋላ ግን ይጾማሉ በማለት አስረድቷ ቸዋል ። ማቴ ፱.፲፬-፲፭ ።

ይህንንም ማለቱ እኔ ወደሰማይ ካረ ግሁኝ በኋላ ጾሙ ማለቱ ነው እንዲ ሁም ማቴ ፲፯ ተጽፎ እንደምንመለከ ተው ሰይጣን ካልጾማችሁ በቀር ሰይጣ ንን ልታወጡ አትችሉም ሲል ለደቀ መዛሙርቱ አስረድቷቸዋል ። በተጨ ማሪም ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳ ዊ አንቀጽ ፲፭ ላይ ብትመለከት በሰ ፊው ለመ ረዳት ትችላለህ ።

፮ኛ መጽሐፍ ቅዱስ ከየት ተገኘ ስላልከው እንደ መናኛውም ዕቃ ከመን ገድ ወድቆ የተገኘ አይደለም ። እግዚአ ብሔር ያደረባቸው ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ የጻፉት ነው እንጂ ይህ ንንም ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲገልጽ “ማንም በገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈ ቀደለትም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱ ስ እየተመሩ ተናገሩ እንጂ ይላል ፪ኛ ጴጥ ፩. ፳፩ ።

በስንት ዓ/ም ተጻፈ ስላልከው የመጻሕፍተ ብሉያት ጽሑፍ የተጀመ ረው በ፫ሺ፭፻፲፮ ዓ/ዓ በሙሴ ጸሐፊነት ሲሆን መጻሕፍተ ሐዲሳት ደግሞ ከክ ርስቶስ ልደት በኋላ በአንደኛው ምዕት ዓመት ነው ። የተጻፉት የጻፎቻቸውም የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረባቸው ሐዋርያት ሰብእ አርድስትና በየጊዜው የተነሡ ሊቃውንት ናቸው ።

# ዜና ሊቃውንት

## የአለቃ አምሳሉ መርሻ አጭር የሕይወት ታሪክ

አለቃ አምሳሉ መርሻ መምህር ዘቤ ተልሔም ከስመ ጥሩው አባታቸው መምህር መርሻ ወልደ ማርያምና ከእና ታቸው ወ/ሮ ጠይም ገብረ ሕይወት በ ጎንደር ሀ/ስብከት ጋይንት አውራጃ በ ምትገኘው ቤተልሔም በ፲፰፻፸፰ ዓ/ ም ጥር ፳፩ ቀን ተወለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከወላጅ አባታቸው ከመምህር መርሻ ትምህርት ጀምረው ንባብ ዳዊት ጾመ ድጓና ምዕራፍ ድጓ በሚገባ ከተማሩ በኋላ የዲቁና መዓር ግን ከአቡነ ማቴዎስ ተቀብለዋል ።

ከዚያም በዚሁ ሀ/ስብከት ወደምትገ ኘው ማኅደረ ማርያም ሂደው ከመም ህር ደስታ ዘንድ የቅኔ ትምህርትን ተም ረዋል ለሁለተኛ ጊዜ ወደሊቦ አውራጃ ሂደው ሚካኤል ደብር ከነበሩት ስመ ጥሩ ሊቅ መምህር ጌቴ ገሞራው ቅኔ ውን ከእነአግባቡ በሚገባ አጠናቀው

ተምረው ወደተወለዱበት ቅድስት ቤተ ልሔም ተመልሰው ከአባታቸው መምህር መርሻ ወልደ ማርያም ቀድሞ የተማሩትን የዜማ ትምህርታቸውን አጠናቀው ተምረው በ፲፱፻፰ ዓ/ም በድ ጓ መምህርነት ተመርቀዋል ።

እንዲሁም በዚሁ አውራጃ ውስጥ በምትገኘው ዙር አባ ጽርሐ አርያም ከነበሩት ከመምህር ኮከብ ዘንድ ዝማሬ ና መስዋዕት አጠናቀው ተምረዋል ። በተጨማሪም አቋቋም ከስመ ጥሩው አለቃ ዓለሙ ከበሴ ዘንድ በሚገባ ተም ረው ለማስተማር ከሚያደርስ ዕውቀት ደርሰው ነበር ።

በ፲፱፻፲፫ ዓ/ም ወደ ሰሜን አውራጃ ሂደው ከደጃዝማች አያሌው ብሩ ጋር ተገናኙ ደጃዝማች አያሌው ብሩም የሊ ቁን አለቃ አምሳሉ መርሻን ከፍተኛ እውቀት ተመልክተው እንዚራራ ተክ ለ ሃይማኖት የተባለውን ታላቅ ደብር እንዲያስተዳድሩ ሹሞቸው ከ፲፱፻፲፫- ፲፱፻፳ ዓ/ም ለሰባት ዓመታት ስሙ በተጠቀሰው ደብር በአልቃና አስተዳ ድረዋል ። በዚህም ጊዜ አለቃ አምሳሉ ከደጃዝማች አያሌው ብሩ ካባና ቀሚስ እስከ ጥንግ ድርቡ ተሸልመዋል ።

በ፲፱፻፳ ዓ/ም ወደ ተወለዱባት ወደ ቤተ ልሔም ተመልሰው የቀራቸውን ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ከአባታ ቸው መምህር መርሻ ወልደ ማርያም እያጠናቀቁ እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ቆይተ ዋል ። በዚሁ ዘመን ስመ ጥሩው አባታ ቸው ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ አለ ቃ አምሳሉ መርሻ በዜማ ትምህርት እጅግ በጣም ከፍ ያለ ዕውቀትና ችሎታ ስለነበራቸው በአባታቸው እግር በመ ተካት የቤተ ልሔም የድጓ ምስክር እን ዲሆኑ ተመርጠዋል ።

በዚህም መሠረት አለቃ አምሳሉ መ ርሻ ለድጓ ምስክርነት ተመርጠው እን ዲያስተምሩ ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው ማስተማር ከጀመሩበት በ ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ወዲህ በንቃትና በትጋት ባዕድ ዘመድ ትንሽ ትልቅ ሳይሉ ሁሉ ንም እንደልጅና እንደወንድም በእኩል ነት ደረጃ በመመልከት ያስተምሩ ነ በር ። አለቃ አምሳሉ በሚያስተምሩት ትምህርት ሁሉ ንዝህላልነትና ቸልተ ኞነት ፈጽሞ የማይታይባቸው ለማስተ ማር የነቁና የተጉ ሊቅ ነበሩ ።

“በነገር ሁሉ መልካምን በማድረግ ምሳሌ የሚሆን ራስህን አሳይ በትምህ ርትም ደኅንነትን ጭምትነትን ጤናማ ና የማይነቀፍ ንግግርን ግለጥ” የሚለ ውን ቃል በተግባር ለመተርጐም ወን በር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው በሚ ያስተምሩበት ሁሉ ደከመኝ ልረፍ ሰለ ቸኝ ልዝናና የማይሉና በጠቅላላው በ ሚያከናውኑት መንፈሳዊ ተግባር ሁሉ



www.ethiopianorthodox.org

ለደቀመዛሙርቶቻቸው መልካም ምሳሌ ለመሆን የሚጥሩ በመሆናቸው በማንኛውም ሰው ዘንድ የነበራቸው ተወዳጅነት እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነበር ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሊቁ አለቃ አምሳሉ መርሻ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “እኮ አንትሙ ዘትነብቡ አላ መንፈሱ ለአቡክሙ ውእቱ ይነበብ በላዕሌክሙ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁም በእናንተ ላይ አድሮ የሚኖር የአብ የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ አድሮ ይናገራል እንጂ ሲል በተናገረው ቃል መሠረት የእግዚአብሔር መንፈስ ያልተለያቸውና የማስተማር መንፈሳዊ ጸጋ ከአምላክ የተሰጣቸው በመሆኑ የድጓ ምልክት ሳይመለከቱ ሲያዜሙ ምልክቶቹ የማይሳሳቷቸው ጥንቁቅ የሆኑ ሊቅ ነበሩ።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሁናችሁ የተወደዳችሁም ሁናችሁ ምሕረትን ርኅራሄን ቸርነትን ትሕትናን የዋ ትዕግሥትን ልበሱ እርስ በእርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ “ያለውን መንፈሳዊ ምክር ተግባራዊ ለማድረግ የተራበውን ማብላት የተጠማውን ማጠጣት የታረዘውን ማልበስ ሐዘንና ጭንቀት የደረሰባቸውን ክርስቲያኖች በየጊዜው ከአጠገባቸው በመገኘት ማጽናናትና መምከር የዘወትር ተግባራቸው ነበር ።

አለቃ አምሳሉ መርሻ ወንበር ዘርግተው ደቀመዛሙርቶቻቸውን በሚያስተምሩበት ጊዜ የተጠየቁትንም ሆነ ያልተጠየቁትን ጠቃሚ የሆነ ትምህርት ያለማመንታትና ያለአንዳች ችግር በሙሉ ድምጻቸው ለደቀ መዛሙርቶቻቸው ለማስረዳት ከፍተኛ ችሎታ የነበራቸው ታላቅ ሊቅ ነበሩ ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕ ፲፪.፴፫ መልካም ዛፍ በፍሬው ይታወቃል ሲል በተናገረው ቃል መሠረት የአለቃ አምሳሉም የዕውቀት ችሎታ የሚለካው ከእርሳቸው ተምረውና አውቀው የዕውቀታቸው መመዘኛ ወረቀት ተቀብለው ሐሩ ወመሐሩ የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ ለመፈጸም ወደየሀገረ ስብከቱ በሚልኳቸው ምሑራን ደቀ መዛሙርቶቻቸው አማካይነት መሆኑን ልንዘነጋው አይገባም አለቃ አምሳሉ ከተማሪዎቻቸው መካከል ፡

ሀ/ በዕድሜ የገፉት ፣ ለ/ ዓይናቸው የተሠወረና በኑሮ ውድነት የተነሣ ተስፋ በማጣት ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ሰርክ ኅብስት እየሰጡ ያለ ችግር ትምህርታቸውን እንዲጨርሱ ያደርጉ ነበር አለቃ አምሳሉ መርሻ ሐዋርያው ጳውሎስ መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል የተጠራህለትንም በብዙ ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንክለትን የዘለዓለምን ሕይወት ያዝ ተብሎ የተናገረውን ቃል በተግባር የተረጐሙና በዚህም የተቀደሰ መንፈሳዊ ሥራቸው ለደቀ መዛሙርቶቻቸው መልካም ምሳሌ የነበሩ ሊቅ መሆናቸው የታወቀነው ይሁን እንጂ አለቃ አምሳሉ ሊቀነታቸውና መንፈሳዊነታቸው በሁሉም ዘንድ የሚያስወድዳቸውና የሚያስመሰግናቸው ቢሆንም ሥጋን ለለበሰ ፍጡር ሁሉ ሞት የማይቀር ስለሆነ አለቃ አምሳሉ መርሻም ከተወለዱ በ፹፬ ማስተማር በጀመሩ በ፷ ዓመታቸው ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው በተወለዱባትና ለብዙ ዓመታት ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው ሲያስተምሩ በነበሩባት ቅድስት ቤተ ልሔም ተቀብረዋል ።

በቀብራቸውም ላይ በሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን በቤተ ልሔም ዙሪያና አካባቢ የሚኖሩ ሊቃውንት በጋይንት አውራጃ ያሉ ምሑራን ተገኝተዋል ።

በአለቃ አምሳሉ መርሻ ዘመን የተፈጸመ የአለቃ አምሳሉ አባት አለቃ መርሻ በሞቱ ጊዜ ወንበሩን ለመያዝ ከአለቃ አምሳሉ ጋር መምህር እንግዳየሁ የተባሉ ምሑር ተወዳድረው ነበር ነገር ግን አለቃ አምሳሉ ብልጫ አግኝተው ወንበሩን ስለያዙ የመምህር እንግዳየሁ ዘመድ የሆኑ ፊታውራሪ በየነ የሚባሉ ሰው በጣም ተናደዱ ከንዴታቸውም የተነሣ የምስክሩን ድጓ በድብቅ ወደቤታቸው ወስደው አስቀመጡት ወዲያው ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ እሳት ተነሥቶ ያንን የተደበቀ ድጓ ገበታው የተሸፈነበትን ጨርቅ ከበላው በኋላ በመጽሐፉ ላይ አንዳችም ጉዳት ሳይደርስበት በመገኘቱ እስከ አሁን ድረስ የድጓ አድራሾች ሁሉ የማስመስከሪያ መዝገብ ሁኖ በአገልግሎት ላይ ይገኛል ። ይህም እግዚአብሔር አምላክ የአለቃ አምሳሉን መምህርነት ፈቅዶ የተቀበለው መሆኑን የሚያስረዳ ነበር ።

ከአለቃ አምሳሉ መርሻ እየተማሩ ድጓ እያስመረቁ በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ተሠራጭተው የሚያስተምሩ መምህራን ስፍር ቁጥር የላቸውም ከአለቃ አምሳሉ ድጓ ያደረሱትን በዝርዝር ለማስፈር ሰፋ ያለ ዓምድን ስለሚጠይቅ ለመጻፍ አልሞከርንም ።

እንደ አለቃ አምሳሉ በትምህርታቸውም ሆነ በጥሩ ሥነ ምግባራቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ያገለገሉና የሚያገለግሉ ሊቃውንት ነበሩ አሁንም አሉ ወደፊትም እንደሚኖሩ ተስፋ እናደርጋለን ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በቅን መንፈስ በማገልገል መዋዕለ ሕይወታቸውን ያሳለፉትን ምሁራን አትዘነጋቸውም ። ስማቸውን ከሕይወት ታሪካቸው ጋር በመመዝገብ ለተከታይ ትውልድ ታስተላልፋለች ።



ከገጽ ፲ የዞረ

አጠጥታችሁኛል እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል ታምሜ መአይታችሁኛልና ብታሰር አስፈትታችሁኛል የሚለውን ቃለ ወንጌል ጠንቅቃ ማወቋ እና መረዳቷ ነው ።

በተለይ አፎምያ ከምድራዊ ክብር ይልቅ ሰማያዊ ክብርን የምታመርጥ ታላቅ አሚኒት በመሆኗ በከንቱ ውዳሴ ሳትጠመድ ከዕለት ተግባሩ ጋር መጾምና መጸለይን የምታዘወትር ደግ ሴት መሆኑዋን አይቶ ሰይጣን ቀናባት እና ተፈታተናት ከዕለታት አንድ ቀን አፎምያ በተመሰጠ ወደ እግዚአብሔር ስትጸልይ ሰይጣን አረጋዊት ሴት መስሎና ብዙ ሴቶችንም አስከትሎ ሂደና አፎምያ ሆይ ጾምሽ . ጸሎትሽ ምጽዋትሽ እጅግ ጥሩ ነው ። ነገር ግን ብትታመሚ የሚአስታምምሽ ብትሞቺ የሚቀብርሽ ልጅም ሆነ ዘመድ ስለሌለሽ ከዚህ አድራጐትሽ ተቆጥበሽ ባል አግብተሽ ልጅ ወልደሽ ሀብት አግኝተሽ በዚህ ዓለም በደስታ ብትኖሪ ይሻላል እያለ ወዳጅ መስሎ መከራት ፅ እሷ ግን ምኞቷ ከዚህ ዓለም ክብርና ብዕል ሳይሆን መንፈሳዊ ክብር አግኝቶ መኖር ስለሆነ ከዲያብሎስ የቀረበላትን የማሰናከያ ቃል ሰለ አልተቀበለችው ከፊቷ ተሰውሮ ጠፋ ።

እንደገናም ይህ ሰይጣን መልኩን በመለወጥ አክሊል ጸፍቶ የወርቅ ዘንግ ይዞ ወደ አፎምያ ሂደና እኔ ከእግዚአብሔር የተላኩኝ ቅዱስ ሚካኤል ነኝ ጾምሽ ጸሎትሽ ምጽዋትሽ አርጐልሻል ። ቅጽመ እግዚአብሔርም ደርሶልሻል ደስ ይበልሽ ። ግን ባል አግብተሽ እንድትኖሪ እግዚአብሔር ንገራት ብሎ አዝዞኛል አላት እሷ ግን የሚስተዋል ስጦታ ስለነበራት በንግግሩ ሳታምን ለመሆኑ ከእግዚአብሔር ያተላክህ መልአክ ከሆንህ ከያዝኸው ብትር ላይ መስቀል ለምን የለበትም ብላ ተንኰሉን ስለገለጠችበት ተናዶ መላእክት መስቀል አይዙም ለዚህ ነው እኔም ያላዝሁት አላት አፎምያም በንግግሩ ርኩስ መንፈስ መሆኑን በማወቋ ልብስህና አስኬማ ጥሩ ነበር ንግግርህ ግን ሰይጣናዊና ከሬትም የመረረ ስለሆነ ምክርህን አልቀበልህም ስላለችው መልአከ ብርሃን መሆኑ ቀርቶ መልአከ ጽልመት ፣ መንፈሳዊ መሆኑ ቀርቶ ሰይጣናዊ ሆና በንዴት ጉረሮዋን አንቃት አፎምያ ከደረሰባት ፈተና ያድናት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየች ጮኸችም እግዚአብሔርም ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ ከዲያብሎስ ፈተና አዳናት ቅዱስ ሚካኤልም ዲያብሎስን ሰይፉን መዝዞ በቀጣው ጊዜ ስምህ በሚጠራበት ሥዕልህ በሚገኝበት አልደርስም ተወኝ ብሎ ስለተናገረ ትቶታል ።

አፎምያም በእግዚአብሔር ኃይልና በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት በራሷም ጽኑ እምነት ከሰይጣን ፈተና በድል አድራጊነት ወጥታለች ከፈተናዋ በኋላ ግን ቅዱስ ሚካኤል ቃል በቃል አነጋገራትና ጾሟ ፣ ጸሎቷ ፣ ቅጽመ እግዚአብሔር በትክክል የደረሰላት መሆኑን ነገራትና ከቤቷ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄደች እንድትጾምና እንድትጸልይ አጽናናት እሷም ለጾምና ለጸሎት ራሷን አስገዝታ ፈጣሪዋን እያገለገለች ከቆየች በኋላ ከዚህ ዓለም ወደዘለዓለማዊ ዓለም ሂዳለች በዘመናችንም ቢሆን እናቶቻችንና እህቶቻችን ጾምና ጸሎት ሲአዘወትሩ ትሩፋት ሲሰሩ ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ በተለያዩ ሁኔታ ሊፈትናቸው ስለሚችል ከአፎምያ ታሪክ ተምረው ማነኛውንም ነገር ፈጥነው ከመቀበላቸው በፊት እያስተውና እየመረመሩ የነገሩን አመጣጥ ቢከታተሉ ከሰይጣን ፈተና በቀላሉ ለመዳን ይችላሉ ።

ሊቀ መዘምራን ተሰማ ገብረ ሚካኤል

## ቆማ ፋሲለደስ ፡

ቆማ ፋሲለደስ የሚገኘው በጎንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ ነው ይህ ታላቅ ደብር የተተከለው በዓፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት በ፲፮፻፲፰ ዓ/ም ሲሆን የተከሉትም እቴጌ ወልደ ሰአላ የዓፄ ሱስንዮስ ባለቤት የዓፄ ፋሲል እናት ናቸው እቴጌይቱ ይህን ስመጥር የሆነ ገዳም ሊያስተክሉ የቻሉበት ምክንያት እንደሚከተለው ነው ።

በዘመናቸው ጠላት ተነሥቶባቸው ለመዋጋት ወደጦርነት ሲሄዱ አንድ ባሕታዊ ወደ እርሳቸው አስገቡኝ ለእቴጌይቱ የምነግራቸው ዓቢይ ጉዳይ አለኝ ብሎ ገብቶ ፋሲለደስ የሚባል ታቦት አምጥተው ቤተ ክርስቲያን አሠርተው በዚያ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም እንዲመሰገን እንዲቀደስና እንዲወደስ ቢያደርጉ በዘመንዎ ሁሉ ሰላም ይሆናል ፣ አሁን የሚሄዱበትንም ጦርነት ድል አድርገው ይመለሳሉ ብሎ ስለነገራቸው ነው ።

እቴጌይቱ ከባሕታዊው የተነገራቸውን ቃል በጽሞና ካዳመጡ በኋላ አሁን ከምሄድበት ጦርነት ጣላቴን ድል አድርጌ በሰላም የተመለስኩኝ እንደሆነ በፋሲለደስ ስም ቤተ ክርስቲያን አሠርቼ በዚያ ታቦቱን አስቀምጬ የእግዚአብሔር ስም እንዲቀደስ እንዲወደስ አደርጋለሁ ብለው ብፅዓት ገብተው ዘመቱ ጠላታቸውን ድል አድርገው ተመለሱ ከተመለሱም በኋላ ባሕታዊው እንደነገራቸው የገቡትን ብፅዓት ላለመፈፀም ብር አደጌ ከተባለ ቦታ ላይ በፋሲለደስ ስም ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ታቦቱን ለማስገባት ሠራዊታቸውን አስከትተው ሄዱና የበዓሉ ዕለት በሬ ሲታረድ በደንብ አንገቱ ሳይቈረጥ በመቅረቱ የታረደው በሬ ከዚያ ቦታ ተነሥቶ በግምት 5 ኪሎሜትር መንገድ ከሔደ በኋላ አሁን የፋሲለደስ ቤተ ክርስቲያን ከታነፀበት ቦታ ሲደርስ ቆመ በዚህ ምክንያት እቴጌ ወልድ ሰአላ የታቦቱ ፈቃድ ከዚህ ቦታ ቢሆን ነው ብለው እንደገና በዚያ ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያኑን አሳንፀው የቦታውንም ስም ቆማ ብለው ሠየሙት ይባላል ።

እቴጌ ወልድ ሰአላ የዚህንን ታላቅ ገዳም ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ከፈ



www.ethiopianorthodox.org

ጾሙ በኋላ እንደሚከተለው ሥርዓት ሠርተዋል ። በቤተ ክርስቲያኑ የተከ ኒቻው ሊቃውንት ብዛት 318 ሲሆኑ ከእነዚህ ሊቃውንት መካከል ።

፵፮ ስብሐተ ነግህ ከዓመት እስከ ዓመት የሚቆሙ መዘምራን

46 ደናግል መነኮሳት የሌሊትና የመ ዓልት ሰዓታት የሚቆሙ ኪዳን የሚ ያደርሱና የሚቀድሱ ።

፷፱ በሰሞንኝነት የሚያገለግሉ

፵፪ ጠባቂዎች ማይ ቀጅዎች ሙጋድ ፈላጮችሰፍሕም አፍሐሚዎች

፳፪ የመሥዋዕት ስንዴ የሚያቀርቡ

፲፪ ጧፍ የሚያጠሙና የሚያቀርቡ

፵፰ ቀራፊዎች አድርገው ሠርተዋል ።

ነዳሙም አስተዳዳሪ የአጉዛ መም ሀር ሲሆን ድንግል መነኩሴ ካልሆነ በስተቀር ሚስቱ ሙታበት የመነኮሰ አይሾምም እንዲቀድስም አይፈቀድለ ትም የገዳሙ አስተዳዳሪ መምህር የሚ ሾመው እንደማኅበረ ሥላሴና እንደዋል ድባ በማኅበረ ካህናትና ምእመናን ነው ።

ይህ ታላቅ ገዳም ቆማ ፋሲለደስ የራ ሱ የድጓ ምስክር አለው ቆሜ ዜማ የተማረ ደቀ መዝሙር ሁሉ የሚያስመ ለክረው ቆማ ፋሲለደስ ነው በአሁኑ ጊዜም ቢሆን ብዙ ደቀ መዛሙርት ነማስመስከር ላይ ይገኛሉ ።

ቆማ ፋሲለደስ ከሚነገርለት ከፍ ተኛ ታሪክ አንዱ ጠላት ኢጣሊያ ሀገ ራችንን ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን ፲፱፻፳ ዓ/ም መስከረም ፲፩ ቀን በዓሉ በሚከበርበት ዕለት የኢትዮጵያ ዓርበ ኞች ዛሬ ቆማ ፋሲለደስን ሊያከብሩ በዚህ ተሰብስበዋል ተብሎ ለጣሊያን የጦር አዛዥ ስለተነገረው ከቀኑ ልክ በ፮ ሰዓት ቅዳሴ ሲቀደስ በአውሮፕላን መጥቶ ፳፮ ቦምብ በቤተ ክርስቲያኑ ላይ እንደዝሃናብ አዘነበ ነገር ግን ፳፮ቱ ም ቦምብ ከቤተ ክርስቲያኑ ጣራ ላይ እያረፈ እንደደንጊያ እየተንከባለለ ከመውደቅ በስተቀር በሰውም ሆነ በቤተ ክርስቲያኑ ዕቃ ላይ አንዳችም ጉዳት አላደረሰም

# የክርስቶስን ዕርገት ያየ ማነው ?

ዕርገት ከታች ወደ ላይ መውጣት ሲሆን ከሰማይ ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖ ረው ክርስቶስ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ርስቶስ ዕርገት በክብር በይባቢ መላእ ክት እና ብዙ ሰዎች እያዩት ሲሆን ከዐ ረገም በኋላ የተቀመጠው በአባቱ ቀኝና በክብሩ ዙፋን ላይ ነው የሄኖክና የኤልያስን ዕርገት የመረመርን እንደ ሆን ሰብአዊ ሆኖ ከቅዱሳን ህላዌ ጋር ተመሳስሎ እናገኛቸዋለን ምንም እንኳ ሲያደርጉ ሰው ቢያያቸውም ያረጉት ከእግዚአብሔር ክብር በማግኘት ሲሆን የተቀመጡትንም በገነት ነው ።

ለምሳሌ ሄኖክን ብናወሳ "ሄኖክ ሞትን እንዳያይ ከምድር ወደ ሰማይ በእ ምነት ተወስዶ እግዚአብሔርም ስለ ወሰደው አልተገኘም ወደ ሰማይ ከማረ ጉም በፊት እግዚአብሔርን በእምነቱና በመልካም ሥራው እንዳስደሰተ ስለተ መሰከረለት ነው" የዕርገትን ዕድል ሊያገኝ የቻለው ነቢዩ ኤልያስም ቢሆን ሁለተኛ ነገሥት ም. ፪ ከቁ ፯ - ፲፪ ብን መለከት በዚያን ዘመን ይኖር የነበረው ህብረተሰብ ተበላሽቶ የነበረው የመን ፈሳዊ ኑሮው አቋም እንዲቃና የፍርድ ጉድለት እንዲስተካከል ሰላም እንዲስ ፋፋ ጋብቻ የፀና ሆኖ መፋታት እንዲ ቀር በጠቅላላ አልጫ የሆነውን ማህበ ራዊውን ኑሮ በትምህርት ካጣፈጠ በኋላ በሚያደርግበትም ጊዜ "ከነቢ ያት ልጆች ሃምሳ ሰዎች ሂደው አዩት ቀጥሎም ኤልያስን ሊሸኘው የተከለ ውን ኤልሳዕን ከአንተ ሳልለይ አድርግ ልህ ዘንድ እምትሻውን ለምን አለው ኤልሳዕም መንፈስህ በእኔ ሁለት እጥፍ ይሆን ዘንድ እለምንሃለሁ ሲል ጠየ ቀው እሱም ከአንተ ዘንድ በተለየሁ ጊዜ ብታየኝ ይሆንልሐል አለዚያ ግን አይሆንልህም ሲል መለሰት ይህንን እየ ተጨዋወቱ ሳሉ የእሳታ ሰረገላና የእ ሳት ፈረሶች በመካከላቸው ገብተው ከፈ ሉዋቸው ኤልያስም ሞልቶ የነበረውን የዮርዳኖስን ባህር ከፍሎ የተሻገረበትን መጎናጸፊያውንና እቃውን ሁሉ ለኤል ሳዕ ሰጥቶ በአውሎ ነፋስ ተነጥቆ ወደ ሰማይ አረገ ። በዚህ ጊዜ አልሳዕም የነ ቢያትም ልጆች አይተውታል ።

የሄኖክና የኤልያስ ዕርገት ይህን ሲመ ስል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መታ የትና ዕርገት እንዲህ ነበር ክርስቶስ በሰጠው ተስፋ መሠረት የሰውን ልጅ ለማዳን ወደዚህ ዓለም ከርደቱ ጀምሮ እስከ እርገቱ ድረስ የሥራው ሥራ ሁሉ በስውርና በምሥጢር ሳይሆን በአደ ባባይና በግልጥ ነው በቤተልሔም ሲወ ለድ የሰማይ መላእክትና እረኞች ሰላም በምድር እያሉ ዘምረውለታል ። እረኞችም እስከ ቤተልሔም ድረስ ሄደ

ይህንን አስደናቂ ታሪክ በሠቀት በበዓሉ አከባበር ላይ የነበሩ ብዙ አዛ ውንት በዓይን ማየታቸውን ይናገራሉ እንዲያውም በዚያ ቀን ከሌላው ጊዜ የበለጠ ሕዝብ ተሰብስቦ ስለነበር የበዓሉ ሁኔታ እጅግ በጣም የደመቀ ነበር በማ ለት የምስክር ቃላቸውን ይሰጣሉ ።

ምእመናን ሆይ ! ይህ ባለታሪክና ዝነኛ ገዳም ተብሎ የሚታወቀው ቦታ በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኑ ክዳን ሣር ከመሆኑ የተነሣ ሕንፃ ቤተ ክርስ ቲያኑ በዝናብ ፍሳሽ ለመፍረስ ተቃርቦ ይገኛል በእርግጥ እቴጌ ወልደ ሰአላ ሲ ያሠሩት በሰው ቁመት ልክ ግንቡ በስ ሚንቶ የተሠራ ሲሆን ከዚያ በላይ በጭ ቃ የተገነባ ነበር ይሁን እንጂ ባሁኑ ጊዜ የመጀመሪያው ሥራ እየፈረሰ ነው ስለዚህ ይህንን ታላቅ ገዳም ቆርቆሮ ለማልበስ ስለታሰበ በአዲስ አበባ ከተማ ኮሚቴ ተቋቁሟል የዚህን ስመ ጥሩና ታላቅ ገዳም ታሪኩን ጠብቆ ለተከ ታይ ትውልድ ለማስተላለፍ ይቻል ዘንድ ከመላው ኢትዮጵያ ምእመናን ኮሚቴው በሰማዕቱ በቅዱስ ፋሲለደስ ስም ርዳታ ይጠይቃል ።

የኮሚቴው አድራሻ ስልክ ቁጥር 11.66.16 የመ/ሣ/ቁ/31.37 አ.አ. መሆኑን እንገልጻለን ።



ው ጎብኝተውታል በዓይናቸውም አይ ተውታል ። የምሥራቅ ሰዎችም ተጉ ዘው መጥተው ከፊቱ ወድቀው ሰግደው ውለታል እጅ መንሻም አቅርበውለ ታል ሠላሳ ዓመት ሲሆነውም በዮርዳ ኖስ ወንዝና በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ወንጌላዊው ሉቃስ በምዕራፍ ፫ ከቁ. ፳፩ - ፳፫ እንደጻፈው "ሕዝቡም ሁሉ



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ሲያርግ

ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስም ደግሞ ተጠመቀ መንፈስ ቅዱስም በአ ርግብ አምሳል ወርዶ በእርሱ ላይ አረፈ. የምወድህ ልጄ አንተ ነህ" በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ" ብሏል ይህም ሲጠመቅ ብዙ ሰዎች እንዳዩትና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድነትእንዳለውና እንደ መሰከሩለት ያስረዳል ።

ወንጌልንም እየተዘዋወረ በሕዝብ መካከል በሚያስተምርበት ወቅት የተ ራቡትን አጥግቧል የተጠሙትን አርከ ቶአል የታመሙትን ፈውሷል የሞቱት ንም አስነሥቷል ።

ይህንን የመሰለውን ቅዱስ ተግባር ከፈጸመ በኋላ መሥዋዕት አድርጎ በሚ ያቀርብበት ወቅት ብዙ መከራ ተቀብ ሏል በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፯ ከቁጥር ፩ - ፳፯ ያለውን ስለመከራው ብናነብ "ሴነጋም የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ሁሉ ሊገድሉት በኢየሱስ ላይ ተማከሩ አስረው ወስደው ወደ ጲላጦስ አቀረቡት እሱም እንደ ሕጋ ቸው እንዲፈጽሙበትና እንደፈለጋ ቸው እንዲቀጡት ለባላጋራዎቹ አሳ ልፎ ሰጠው እነሱም የሚሰቀልበትን መስቀል አሸከመው ወሰደው ሰቀሉት የከተማውና የአካባቢው ሕዝብ በአ ዋጅ እንዲመለከተው ተደረገ ከሞተም በኋላ ባለጸጋው ዮሴፍ ጲላጦስን ለምኖ የክርስቶስን ሥጋ በራሱ መቃብር ቀብ ረው የአይሁድ ሊቃነ ካህናትና ሽማግ ሌዎችም ይነሣል ብለው ስለፈሩ ከጲላ ጦስ ጋር ተማክረው በማህተም መቃብሩን አተሙት" የገዛ ዘበ ኞቻቸውንም እስከ ሦስት ቀን ድረስ እንዲጠብቁ አዘዙ ።

ክርስቶስም በሦስተኛው ቀን ሲነሣ በመቃብሩ ዙሪያ ምድር ተናውጦ ብር ሃንም በራ በዚህ ጊዜ ጠባቂዎችም ደንግጠው እንደበድን ሆኑ ክርስቶስ ግን ከሞት ተነሥቶ እየተመላለሰ ሰላም ለናንተ ይሁን እያለ ተገልጾ አነጋገራ ቸው ከነሱም ጋር አብሮ ምሳ በላ እንዲሰ ብኩና እንዲያስተምሩ ሥልጣን ሰጣቸው መጽሐፉንም ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአ ቸውን ከፈተላቸው ።

የሚያርግበትም ቀን ስለደረሰ እነ ሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክ ላችኋለሁ እናንተ ግን ከላይ ኃይል ስለ እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተ ማ ቆዩ አላቸው ። ቀጥሎም ከይሁዳ በቀር 120 የሆኑ ደቀ መዛሙርትን ወደ ደብረ ዘይት ይዟቸው ወጣ አንድ ላይም ተሰበሰቡ በመጨረሻም የሚከተ ለውን የሰንበት ቃል ነገራቸው መን ፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳ ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳር ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ ። ይህንንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩ ከፍ ከፍ አለ ደመናው ተቀበላቸው እነርሱም ሲሄድ ወደሰማይ ትኩር ብ ለው ሲአመለከቱ ሳለ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባ ቸው ቆመው ነበር እናንተ የገሊላ ሰዎች ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ከዚህ ለምን ቆማችሁ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው እየሱስ እንዲሁ ይመጣል አለ ዋቸው እነሱም ከደብረ ዘይት ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ክርስቶስም ሰዎች እያዩት ሥራውን ከፈጸመና አገልግሎቱን ካከናወነ በኋላ ወደ ሰማይ እንዳረገ ተብራርቶአል ። የስነ ጽሑፍ የሥዕል ምሑሩና ሐኪም የነበረው ወን ጌላዊ ሉቃስ ክርስቶስ እንዴት እንዳ



www.ethiopianorthodox.org

ረገና በየትኛው ቦታ እርገቱ እንደተፈጸመ ደቀ መዛሙርቱም በሥፍራው ተገኝተው እንደተሰነባበቱ መላእክትም ተከፋይ እንደነበሩ በሐዋርያት ሥራ በምዕራፍ 1 እንዲሁ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፬ ከቁ. ፵፭ - ፶፫ ጽፎ ለትውልድ ሉቃስ ክርስቶስ እንዴት እንዳረገ ለትውልድና ለታሪክ አስተላልፎአል ።

እንዲህ ክርስቶስ የሞትን ኃይል ድል ነሥቶ ከተነሣ በኋላ ሰዎች እያዩት እንዳረገ ተመልክተናል ያረገውም እኛን በማዕረግና በክብር ከፍ ከፍ ሊያደርገን ነው እንደሥራችን እንደ አገልግሎታችንም መጠን ወደሱ ሊስበን ነው ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በምዕራፍ ፪ በቁጥር ፳ "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል አሁንም በሥጋ የምንኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው" ሲል አስተምሯል ።

ይህ ትምህርት የሁላችን ሕይወት የሚመለከት ነው ሐዋርያው እንዳለው ክርስቶስ በእኛ ክኖረ እኛ ከኃጢአት ሁሉ መራቅ ያስፈልገናል ። ይህም ማለት የሥጋ ምኞችና ስስትን የራሳችንን መንገድ መከተላችንን በግል ራሳችንን ብቻ የሚያስደስተንን መፈለግ ሁሉ ራሳችንን ከፍ ማድረጋችን በሌሎች ላይ መቅናትና ሁሉን ማጥፋት ይኖርብናል ። ማለት ነው ምንም እንኳን ይህንን ማድረግ እንደ መስቀል ሞት ከብዶ ቢታየንም ከነዚህ ነገሮች ካልተለየን በክርስቶስ ሕያው መሆንና የዕርገቱ ተካፋይ የመሆን ዕድል አናገኝም ።

ስለዚህ ክርስቶስ ካረገ በኋላ በመስቀል ላይ የሠራው የመሥዋዕት ሥራ ሁሉ ፍጹምና ተወዳጅ እንደሆነ ሁሉ እኛም ሥራችንና አገልግሎታችን ባረገው በክርስቶስ ዘንድ ቸተወዳጅ እንዲሆን ጠንክረን እንሥራ ።

ከአለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ርደተ መንፈስ ቅዱስ

የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ አንድ ታላቅ ተስፋ ሰጥቷቸው ነበር የሰጣቸውም ተስፋ እንደሚከተለው ነው "እነሆ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ "ሉቃ ፳፬ ፣ ፵፱ የሚል ነበር ።

ደቀ መዛሙርቱም ይህንን ተስፋ ሰምተው ከአብ የሚሰጠውን ተስፋ እየተጠባበቁ ክቆዩ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተነሣ በአምሳኛይቱ ቀን ሁሉም ማለት ፲፪ ሐዋርያት በአንድነት ከአንድ ቤት ተሰብስበው ሳሉ ሳያውቁና የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ሳንገነዘቡ በድንገት በእያንዳንዳቸው ራስ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ወረደላቸው ።

ሲወርድ እንደ ዓውሎ ነፋስ ድምፅ እያሰማ ነበር በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ቅዱስ ስለተሞሉ እያንዳንዳቸው በ72 ቋንቋ ለመናገር በቁ ፸፪ ቋንቋ ተገለጠላቸው ከዚያ በኋላ በስማ በለው መናገር ፣ እገሌ የቋንቋ ችሎታ አለውና ያስተርጉምልን ብለው ሰውን ሳይለማመጡ ለተሰበሰበው ሁሉ ያስተምሩ ጀመር ።

በተሰበሰቡበትም ቦታ ቋንቋቸው የተለያዩና ከብዙ አህጉር የተሰሰቡ ሕዝብ ስለነበሩ ለሁሉም በየቋንቋቸው ሲመልሱላቸው ባዩ ጊዜ እጅግ ይደነቁ ነበር ።

ምክንያቱም ከጳንጦስና ከገላትያ ከቀጰዶቅያና ከእስያ እንደዚሁም ከቤታንያ ከጳርቴና ከሜዶን ፣ የተሰሰበ ሕዝብ ሲሆን ለዚህ ሁሉ በየቋየቋቸው ሲመልሱለት በታዩ ጊዜ ታላቅ ተአምርና አስደናቂ ነገር ስለ ተገኘ ሁሉም በአንክሮ ደስ ይሰኙ ነበር ።

ይሁን እንጂ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ነገሩ ዕንግዳ ነገር ስለሆነባቸው እነዚህ ሰዎች ከሌላ ሀገር የመጡ ሳይሆኑ እኛ የምናውቃቸው የገላትያ ሰዎች አይደሉምን እንዴት በባዕድ ቋንቋ ሊናገሩ ቻሉ ወደ ሌላ ሀገር ሄደው ቋንቋውን ተምረዋል ፣ እንዳይባል ከሀገራቸው አልወጡም አብረውን ነው የኖሩ ።

ቀድሞ ተምረዋል ቋንቋውን ያውቁታል እንዳልን ደግሞ እንዳልተማሩና ቋንቋውን እንደሚያውቁ በሚገባ እናውቃቸዋለን ።

እንዴት ባሁኑ ሰዓት በመላ ዓለም በሚገኘው ቋንቋ ይናገራሉ ? በማለት ነገሩ ግራ ሆንባቸው ነገር ግን ከመካከላቸው አዋቂዎች ነን ባዮች አንዳንድ ሰዎች ዝም በሏቸው እነዚህ ሰዎች ሰክረው የሆነውንና ያልሆነውን ይቀባጥራሉ እንጂ የሚናገሩት ነገር ሁሉ ቁም ነገር የለውም እያሉ ይዘብቱባቸው ጀመር ።

ቢሆንም ጊዜው መጠጥ ተጠጥቶ የሚሰከርበት ወቅት ባለመሆኑ ተቀባይነት አልነበረውም ምክንያቱም ጊዜው ከጥዋቱ ፫ ሰዓት ያህል ነበርና ነው ።

ሐዋርያት ዓላማውያኑን ሳይፈሩ ከሐዲዎችንም ሳያፍሩ የሰይፍን ልሳን ኢምንት ሳይቆጥሩ ወንጌልን በትክክለኛ መንገድ ሊያስተምሩ የቻሉ ሰማያዊ ኃይልንና ሰማያዊ ጸጋን ካገኙ በኋላ ነው ። ከዚያ በፊት የተስተካከለ መንፈስ ስላልነበራቸው ሲናገሩ ይፈሩ ነበር ለማስተማርም ቢሆን ያፍሩ ነበር አርያማዊ ኃይልን ካገኙና ከለበሱ በኋላ ግን ፍሩሃን የነበሩት ጥቡአን ሁኗል ።

ከጌታ ስቅለት በፊትማ ወንጌልን ማስተማሩ ቀርቶ ደፍረው መናገርስ መቼ ይችሉ ነበር ። እንዲያውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ወቅት ልብሳቸውን ጥለው የሸሹ ጌታቸውንም ትተው የተበተኑ እንደ ነበሩ ቅዱስ ወንጌል ያስረዳል ከዚያም አልፎ ተርፎ አንተ የኢየሱስ ወገን አይደለህምን ብለው ሲጠይቋቸው እንኳን እረ አናውቀውም እንደዚህ ይሰንጥረን እንደ እንጨት ይሰበረን ብለው የማሉ እንደ ነበሩ ሳንጠቅሰው አናልፍም ነገር ግን ሰማያዊ ኃይልን ከለበሱና





የአቡነ ዓቢየ እግዚእ ታሪክና ገድል በመላ ኢትዮጵያ ባይታወቅም ጻድቁ ብዙ ገድልና ትሩፋት የሠራ መሆኑ መጽሐፈ ገድሉ ያስረዳል የዚህ ጻድቅ ገዳም የሚገኘው በትግራይ ክፍለ ሀገር በተምቤን አውራጃ ከርእሰ ከተማው

አርያማዊ ጸጊን ከተጐናጸፉ በኋላ በረቱ ከብልየት ታደሱ በአእምሮም ጐለመሱ ። ሰማያዊ ኃይልን ሳይለብሱ ግን በክርስቶስ ላይ የደረሰሬ ጸዋትወ መከራ በእኛም ላይ እንዳይደርስብን ብለው ቤታቸውን ዘግተው ከሰውም ዓይን ተሠውረው የነበሩት እነሆ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በመቀበላቸው የሞት ግርማ የማያስፈራቸው የሰይፍ ልሳን የማያስደነግጣቸው ሁነው ከመገኘታቸውም በላይ ከክርስቶስ ጋር ለመኖር ሞትን የሚናፍቁ ሁኖዋል ።

ወንጌልንም በሚያስተምሩበት ጊዜ ረሀቡን ጽሙን ታግሠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ ተቀብለው እርሱን መስለው ሲያስተምሩ ራሱ የክብር ባለቤት ክርስቶስ ምስክሮች ትሆኑኛላችሁ ባላቸው መሠረት እውነተኞቹ የወንጌል ምስክሮች ሁነው ተገኙ ዓለሙም ሁሉ በትምህርታቸው ተሞላ ።

እነሆ ወንጌልን እንግበው የመንፈስንም ሰይፍ ታጥቀው ባስተማሩት መሠረት በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች የቅዱሳን የሐዋርያት ትምህርት ውጤት ነው ።

መንፈስ ቅዱስ ያልተዋሃደውና መንፈስ ቅዱስ ያላደረበት ምዕመን መንፈሳዊ ኃይል የለውም ። ቢናገር ተሰሚነት ፣ ቢያስተምር ተደማጭነት አያገኝም መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ግን በሚያስተምርበት ጊዜ አድማጭና ተቀባይ ከማግኘቱም ሌላ በደረሰበት መንፈስ ቅዱስም ታላላቅ ኃይልን ማድረግ ይችላል ።

በስተሰሜን ምሥራቅ ነው አቡነ ዓቢየ እግዚእ ተወልዶ ያደረገው በዚሁ ሥፍራ ነው የቦታው ልዩ ስም "መረታ" ይባላል ።

አቡነ ዓቢየ እግዚእ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ትሑት ቅንና ርኅሩህ ሰውን አክባሪ እግዚአብሔርን ፈሪ እውነተኛና ሐቀኛ ነበር በዚሁ በመረታ ከነበሩት የሃይማኖት መምህር ከፊደል እስከ ጸዋትወ ዜማ ትምህርቱን አጠናቅአል ። ከዚህም በቀር በሌሎች አውራጃዎችና ወረዳዎች እየተዘዋወረ ትርጓሜ መጻሕፍትን በሚገባ ተምሮአል ።

ወላጆቹ ለአቅመ አዳም መድረሱን አይተው ሊድሩት ፈለጉና አስቀድመው ፈቃዱ እንደሆነ ጠየቁት እርሱ ግን ለማግባት ፍጹም ፍላጎት እንደሌለው ገለጸላቸው ወላጆቹም በዘመድ በአዝማድ እሺ እንዲል አስለመኑት ይሁን እንጂ አቡነ ዓቢየ እግዚእ አንድ ጊዜ ራሴን ለክርስቶስ አሳጭቻለሁና አይሆንልኝም አለ ።

እንደሀገሩ ልማድ ምንም እንኳ ፈቃዱ እንደሆነ ሰውየው በመጀመሪያ ቢጠየቅም እምቢ ካለ ምን አገባህና ተብሎ በተጽእኖ ነው የሚዳረውና ያለፈቃዱ ሚስት አጨለት አቡነ ዓቢየ እግዚእም ነገሩ እየከረረ መሄዱን በተረዳ ጊዜ ጠፍቶ ወደ ሰሜን አውራጃ ሄዶ ተደበቀ ትምህርቱንም የቀጠለ ብዙ ዘመን አሳለፈ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር መልአክ አንድ ጊዜ ገድል የምትቀበለው ትሩፋት የምትፈጽምበት በመረታ ስለሆነ ወደ ትውልድ ሥፍራህ ሂድ ሲል በራእይ ነገረው ።

አቡነ ዓቢየ እግዚእም ከነበረበት እንደተመለሰ በዚያን ጊዜ አባት እናቱ በሞት ከዚህ ዓለም ተለይተው ስለቆዩ ለመንፈሳዊ አገልግሎቱ የተቃና ሆነለት የመረታ ምዕመናን ውኃ የሚቀዳው በጣም ሩቅ ከሆነ ቦታ ነው ስለዚህ አቡነ ዓቢየ እግዚእ ውኃ ቀድተው በተራራው የሚኀዙትን ሰዎች እንስራ ቸውን እየተሸከመ እስከ ሜዳው ድረስ በማድረስ ነበር ገድሉን የጀመረው ።

ይህም ተግርር ለተወሰነ ጊዜ ሳይሆን ከጥዋት እስከ ማታ ነበር ምዕመናኑን ሲያገለግል የሚውለው እንደዚሁም እንጨት የሚሸከሙትንም በዚሁ ተመሳሳይ ይረዳቸው ነበር ማታ ሲሆን ግን በመንደሩ ቢፈለግ አይገኝም ምዕመኑ ወሮታ ሊመልስለት የት እንደሚገኝ ቢያስፈልገው የሚያድርበት ሥፍራ የት እንደሆነ እንድም ለማወቅ አይችልም ነበር ። ጻድቃን ከሚባል ብዙ ጎቡንን ላሉበት እየሄደ ያድር ነበር ።

የመረታ ምዕመናን አቡነ ዓቢየ እግዚእን ከገድሉና ከትሩፋቱ ለማደናቀፍ ብዙ የተለያዩ ወጥመዶች ዘረጉበት ከዋለበት አናውል ካደረበት አናሳድር አሉት ደበደቡት በልዩ ልዩ ሥቃይም አሰቃዩት እንዲሰደድም አደረጉት ።

አቡነ ዓቢየ እግዚእ መረታን ለቆ ወደ ዋልድባ ሄደ በዋልድባም አያሌ ዓመታት በብሕትውናና በትሕርምት ኖረ ከዚያም የእግዚአብሔር መልአክ በሌሊት ተገልጾ የምትቀበለው ገድል (ትሩፋት) በዋልድባ አይደለም ወደ መረታ ተመልሰህ ቅዱስ ወንጌልን በማስተማር የሚመጣብህም ገድል በአኰቴትና በምስጋና እየተቀበልህ ፈጣሪህን ማገልገል ይገባሃል አለው እርሱም እኔስ የመረታ ምዕመናን ክፋትና ጭካኔ ስላስመረረኝ ለመመመለስ ፈቃደኛ አይደለሁም አለ ።

አቡነ ዓቢየ እግዚእ አልሄድም ብሎ በዋልድባ ትንሽ እንደቆየ አንድ ቀን ሌሊት ተኝቶ ሳለ በጥበበ እግዚአብሔር ያች የነበረባት ቦታ ተነሥታ ከዓቢየ እግዚእ ጋር ወደ መረታ መጥታለችኀህ ሲቀድ አቡነ ዓቢየ እግዚእ ከእንቅልፉ ነቃ የወፎች ድምፅ ሰማ በዚህ ጊዜ አቡነ ዓቢየ እግዚእ የዎፎች ድምፅ የመሬት ዎፎች እንጂ የዋልድባ ዎፎች ድምፅ ሁኖ አላገኘውም በዚህ ምክን ያትም ይደነቅና ይገረም ጀመር የት ነው ያለሁት በውኔ ነው ወይስ በሕልሜ አለ ተነሥቶ ጎጆውን ቢመለከተው ያው የዋልድባ ቤቱ ነው ወጥቶ ደጁን ቢያየው ያው የዋልድባ



www.ethiopianorthodox.org

ምድር ነው ። ትንሽ እለፍ ብሎ ቢመለከት ደግሞ የመሬት ምድር ሆኖ አገኘው ።

እግዚአብሔር እልሄድም ብለው በማይመረመር ጥበቡ ካመጣኸኝ ምን አደርጋለሁ ከመሬት ምዕመናን እንግዲህ መከራ እየተቀበልሁ መኖር ነው እንጂ አለ ። አቡነ ዓቢየ እግዚእ በመሬት እንዳይቀመጥ አማኒያኑ በልዩ ልዩ መንገድ እየተነሣ እንዲያሰቃየው ይገፋፋውና ይቀሰቅሰው የነበረው ዲያብሎስ ስለሆነ አሁንም አብየ እግዚእ እንደገና ወደመሬት መምጣቱን አይቶ በልዩ ልዩ ተንኰልእንዲነሣ ይገፋፋቸው ጀመር ።

አቡነ ዓቢየ እግዚእ ግን በየጊዜው የሚፈታተነው ዲያብሎስ መሆኑን ስላወቀ በጸሎት ኃይል ድል ለመንሣት ታጥቆ ተነሣ በዚሁ ጊዜ መልአከ እግዚአብሔር ተገልጾ የእግዚአብሔር ወዳጅ ዓቢየ እግዚእ ሆይ በርታ ጠላትህ ዲያብሎስ ከዚህች ሥፍራ ጓዙን ጠቅልሎ የሚጠፋበት ጊዜ ቀርቦአልና አትፍራ ሰብአ መሬት በሚያመጡብህ ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራም አትሰቀቅ አለው።

አቡነ ዓቢየ እግዚእም የመልአኩን ቃል ተቀብሎ ሥቃዩን ችሎ በምግባር በገድል ጸና ። ስለዚህም ከሰብአመሬት አብዛኛዎቹ ወደ እርሱ እየመጡ አባታችን ዓቢየ እግዚእ ሆይ በድለንሃልና ይቅር በለን እያሉ ከእግሩ ወድቀ በየጊዜው እየመጡ ይቅርታን የሚጠይቁትም እየበዙ ሄዱ ።

የክርስቲያኖች ጠላት የሆነው ዲያብሎስም የዓቢየ እግዚእን በተጋድሎ መጽናት የመሬታን ሕዝብ ወደመንፈሳዊ ጐዳና ማዘንበላቸው በተመለከተ ጊዜ ውዬው ጠፋሁ ከእንግዲህ ወዲህ ማደሪያ መኖሪያ የለኝም እያለ ሲጮህ ተሰማ አቡነ ዓቢየ እግዚእም በጾም በጸሎት በሰጊድና በትሕርምት በመጽናቱ ዲያብሎስን ከሰብአ መሬታ አውጥቶ አባረረው ምዕመናንም በትምህርተ ወንጌል አደሰው የክርስቶስን ገንዘብ አደረገው ።

አቡነ ዓቢየ እግዚእ ከብዙ ተጋድሎ በኋላ ዕለተ ሞቱ ስለደረሰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ሰጠው ወዳጄ ዓቢየ እግዚእ ሆይ በዚህ ዓለም ጥቅም ሳትጠመድ የእግዚአብሔር አገልጋይ ለመሆን ከሕፃንነትህ ጀምሮ እስከ ሕቅታ ድረስ የተቀበልኸው መከራ ሁሉ በማሰብ ሰርአ መሬታን አሥራት አድርጌ ሰጥቻለሁ በዚህች በመሬታ አካባቢ ባሉት ዋሻዎች በአማላጅነትህ አምነው የሚቀበሩት ሁሉ እስከ ዕለተ ምፅዓት ሥጋቸው አይበሰብስም ፣ አጥንታቸው አይፈርስም ፣ ያበደ ውሻ የነከሰው ሰው ከዚህ ጠበልህ በውኃ በጥብጦ ቢጠጣ መጽሐፈ ገድልህ ቢደገምለት ምንም አይነካውም ካንተ በኋላ በዚህች በመሬታ ዙሪያ እልፍ አእላፋት ጻድቃን ይሰበሰባሉ በስምህም ተማጽነው የክብር አክሊል ይቀዳጃሉ ።

ከእንግዲህ ወዲህ በዚህ ዓለም የምትቀበለው ጸዋትወ መከራ ይበትሃል ወደ ዘለዓለም ዕረፍትሕም ግባ አለው ወዲያውም ግን ቦት ፲፱ ቀን መላእክት ብርሃን መጥተው የቅዱሱን የአቡነ ዓቢየ ነፍስ በብርሃን አጀበዋት ወደ ሰማይ አረጉ ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብም አጠገብ አኖሩአት በዚሁም መሠረት ቤ/ ክርስቲያናችን የአቡነ ዓቢየ እግዚእን በዓለ ዕረፍት ግንቦት ፲፱ ቀን በየዓመቱ ታከብራለች ።

ሊ.ት/ ገብረ ክርስቶስ ኃ/ ማርያም

# ጥንታውያት ሴቶች እና ባህላቸው

የባህል ነገር ሲነሳ ብሔራዊ ስሜትን ሲቀሰቅስም ጥሩውን ባህል ከመጥፎ መለየት ያስፈልጋል ። ይህም ሲባል ከአዳም እስከ ክርስቶስ ልደት ይኖሩ የነበሩትን መንሳዊያት እናቶችን እና የዕምነት ሴቶችን ስናስታውስ በጣም በርከት ያሉ ናቸው ። በአይነ ሕሊና አተኩረን ታሪካቸውን ብንመለከት ጥሩ ባሕልን ከግብረ ገብነት ጋር ከታሪካቸው ለመማር እንችላለን ።

ከነዚህ መካከል እንደ እነ ሣራ እንደ ሳሙኤል እናት ሐናን ፣ የዘካርያስ ባለቤት የነበረችውን ኤልሳቤጥን ለምሳሌ እንጠቅሳለን ። ይኸውም ሣራ አብርሃም በችግር ጊዜ ወደ ግብጽ ቢሰደድ ከባለቤቷ ሳትለይ የመከራው ተካፋይ በመሆን አብራ ከመሰደዷም ሌላ ብሔራዊ የሆነውን ልብስን አለወጠችም።

በሚያንጸባርቀው በግብጽ የልብስ አይነት ተማርካ አልተለወጠችም ባሏን አልከዳችም እንኳንስ የባለስልጣኖች ድላላና ስጦታ ቀርቶ የፈርኦን ሽልማት ስጦታ አላታለላትም በእክብሮትም በኩል ብንመለከት ጌታዬ እያለች በቅን ከመታዘዝም ሌላ እራስዋ ታዛ ሌሎችም እንዲታዘዙ ጥሩ የመታዘዝ ባሕል ታሳይ ነበር ።

በእንግዳ አቀባበል በኩል የነበራት ሥነ ስርዓት እና የመስተንግዶ አቀራረብ ለቤተሰቦቿም ሆነ ለሚመለከታት ሁሉ ጥሩ ምሳሌነቷን አሣይታለች ከደግነቷ የተነሣ ሥላሴ ከቤቷ በእንግድነት እንደገቡ ታላቁ መጽሐፍ ይነግረናል ። በዚህም በረከት አግኝታ ይስሐቅን ያህል ልጅ እስከመውለድ ደርሳለች በመጨረሻም ሙሉካም የባሕል ምግባር በየጊዜው ለምንነሣው አማኝ ሴቶች ሁሉ ታላቅ ትምህርት ሲሰጠን ይኖራል ።

ሐናም ብትሆን ሳሙኤል የተባለውን ልጅዋን በሥነ ሥርዓት እየተማረ እንዲያድግ ለሊቀ ካህናቱ ወስዳ ሰጠች ልጁ በሥነሥርዓት እየተማረ ስላደገ እርሷ እንዳሰበችው ለአይሁድ ህብረተሰብ ሊቀ ካህናት ሁኖ ተሾመ ፍርድ አዋቂና መልካም አስተዳዳሪ ሆነ ይህም ሐና ለልጇ ያሳየችው ጥሩምሳሌነት አማኞች የሆንን ሴቶች ሁሉ ልጆቻችን እያስተማርን በሥነ ሥርዓት እንድናሳድግ ያስተምረናል ጥሩ ባሕል ስለሆነ ልንወርሰው ያስፈልገናል ።

ኤልሳቤጥም ብትሆን በተግባር በኩል የነዚህ ተመሳሳይ ስለሆነች እነዚህም ሆኑ ሌሎች ጥሩ ባህል እየተውልን ስላለፉ ልንጠቀምበት ይገባል ።

ይህ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው የተነሱትን የዕምነትና የምግባር እናቶች ለኢኰኖሚና ለልማት እድገት ሲባል በሥራ ገበታ ላይ የፈጸሙት ተጋድሎ ከሕብረተሰቡም ሲወርድ ሲዋረድ የሚገኘውን የሥራ ልምድና እውቀት የሚያጠቃልል ነው ።

ይህም ሲባል ጥንታውያት ሴቶች ጥሩ ባሕል ነው የምንለው ከባለቤቶቻቸው ጋር የሚያሳዩት ጥሩ ኑሮ ለጐረቤታቸውም የሚያሣዩት ጥሩ ምግባር ከሰዎች ጋር የነበራቸው መግባባት በዘር ጊዜም በሕብረት እንስራ በማለት ባለቤታቸው በሬውን እየነዱ ወደ እርሻ ሲሔዱ እነርሱም ዘሩን በአህያ ጭነው ሞፈሩንና ቀንበሩን ተሸክመው ይጓዛሉ በሬም ያጠምዳሉ እርሱ ሲዘራ ጉልጓሎ ይጐለጉላሉ አብረው ያርማሉ አረምም በርከት ብሎ ባስቸገረ ጊዜ ጠላ ጠምቀው እንጀራ ጋግረው በወንፈል እንዲታረም ያደርጋሉ በጠቅላላው አዝመራ ቤት እስከ ገባ ድረስ የሥራው ተካፋይ ይሆናሉ ።

ቀደም ብለው ይኖሩ የነበሩት መንፈሳውያት እናቶቻችን አክብሮታቸውም ሆነ ትዝታቸው ጥሩ ባሕላቸውም ይህ ብቻ አይደለም ።

በመንፈሳዊ ረገድ የተመለከትን እንደሆነ ጥሩ ጥሩ ባሕል ትተውልን እንዳለፉ እንረዳለን ይኸውም የልብስ አለባበስ በሥራ ጊዜ የሚለበስ በሰርግም ፡ ጊዜ ፡ ቤተክርስቲያን በሚሄዱበት ጊዜ የሚለብሱት ልብስ የተለያየ ነበር ። ቤተ ክርስቲያን በሚሄዱበት ጊዜ እራሳቸውን ተከናንበው ነጠላቸውን እንደ መስቀለኛ አጣፍተው ይሄዳሉ ። ከዚያም ለሀገራቸው ፣ ለቤተሰባቸው ለጐረቤቶቻቸው ይጸልያሉ ቢቻላቸው ይቆርባሉ ይህ ባይሆን የቅዳሴ ፀበል ጠጥተው ትምህርት ሰምተው ወደ የቤታቸው ይመለሳሉ ይህንን መንፈሳዊ ሥራቸውን ልጆቻቸው ከልጅነታቸው ጀምረው እንዲውቁና እንዲማሩ ከእነርሱ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን እየወሰዱ ሥነ ሥርዓቱን እያጠኑና እንዲለማመዱ ያደርጓቸዋል ። ልጆቹም የቤተ ክርስቲያን ፍቅር ስለሚያድርባቸው ከፍ ሲል ማንም ሳያስገድዳቸው ከወላጆቻቸው እየጠፉ የቆሎ ተማሪ ሁነው ለረጅም ጊዜ ከዘመዶቻቸው ተለይተው ይኖራሉ ። ተምረውም ከጨረሱ በኋላ በየሙያቸው ቤተ ክርስቲያንና አገርን ያገለግላሉ በተለይም ከላይ የጠቀስናቸው እናቶች የሰንበትን በዓል አከባበር ጥሩ የባህል ማህደር አድርገው አቆይተውናል እረፍት እንድትሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠችንን ይህችን ቀን ጠዋት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂደው የጸሎቱና የቅዳሴው የትምህርቱ ተካፋይ ሁነው ወደ ቤታቸው ተመልሰው ቁርስ ይበላሉ ይህን ከፈጸሙ በኋላ በሽተኞችን በመጠየቅ ፣ ያዘኑትን በማጽናናት የተራቡትንና የተቸገሩትን በመጐብኘት እንግዶችን በመቀበል የተጣሉትን በማስታረቅ በጠቅላላው ይህንና ይህን የመሳሰለውን ምግባረ ሠናይ በመሥራት ቀኑን ያሳልፉታል ።

በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ እነዚህ እናቶቻችን እያበሉና እያጠጡ እያለበሱ ብቻ ሳይሆን አስተማሪም ነበሩ እንደ አሁኑ ጊዜ ምውእለ ህፃናት ስላልነበር አለባበስን ፣ አመጋገብን እንግዳ ሲመጣ ተነስቶ መቀበልን አዋቂዎች ሲጫወቱ ጣልቃ አለመግባትን እናትን እና አባትን ማክበር ብቻ ሳይሆን ትንሹም ትልቁም ማክበር ከእራት በኋላ እሳት እየሞቁ የሀገርን ፍቅር የጀግንነትን ወኔ የያዘውን ተረት እየተረቱ ምሳሌ እየመሰሉ እንቆቅልሽ እያጫወቱ ጥሩውን ባሕል ይዘው እንዲያድጉ ያደርጓቸዋል ።

ልጆቻቸውን እያሳደጉ በሰላም እና በፍቅር ይኖራሉ መጥፎ ባሕል የሃገር እና የትውልድ ጠንቅ ስለሆነ ጥሩውን ባሕል እንደ እናቶቻችን መርጠን እንያዝ ።

ወ/ት ዘነበች ጥላዬ

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ይህችን ዓለም እግዚአብሔር ለሰብአዊ ፍጡር የሰጠው እስከ ተወሰነለት ዕድሜው ድረስ እየሠራ እንዲጠቀምባት መንፈሳዊ ሆነ ሥጋዊውን ሥራ ሠርቶም ክብር እንዲያገኝባት ነው እንጂ እጁንና እግሩን አጣምሮና ሥራንም ፈትቶ እንዲኖርባት አይደለም ።

ስለዚህ ባሁኑ ልማት በቤተ ክርስቲያናችን በወለጋ ሀገረ ስብከት በአሶሳ አውራጃ ስለ ሚካሄደው ልማት እንዴት እንደሆነ መልአከ ኃይል እንየው ውቤን ጠይቀናቸው ነበር ።

ትንሣኤ ፣ የአሶሳ አውራጃ ሰባኬ ወንጌል እንደ መሆንዎ መጠን በዚያ ውስጥ ያሉትንም አብያተ ክርስቲያናት ምን ያህል ብዛት እንዳላቸው ያውቋቸዋል ። ስለዚህ የአብያተ ክርስቲያናቱ ብዛት ምን ያህል እንደሆኑ ቢገልጹልን።

መልስ ፣ በአሶሳ አውራጃ በጠቅላላ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ብዛት 33 ይሆናሉ ይሁን እንጂ ከእነዚህ 33 አብያተ ክርስቲያናት መካከል 15ቱ ከ74 ወዲህ የተሠሩ ናቸው ።

ትንሣኤ ፦ ከ፲፱፻፸፬ ዓ/ም ወዲህ ፲፭ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት ሊሠሩ ቻሉ ?

መልስ ፦ ከዚያ በፊት በረሐ ስለነበርና ምእመናን በብዛት ስላልነበሩበት ነው ከ፸፱ ዓ/ም ወዲህ ግን ከወሎና ከትግራይ አህጉረ ስብከት ስለሰፈሩበትና ግማሾቹ ክርስቲያኖች በመሆናቸው እንደመጡ በየሰፈሩበት ሁሉ ፲፭ አብያተ ክርስቲያናት ሊተክሉ ችለዋል ። እነዚህ በሰፈራ ያሉ ሰዎችም ማንም ሳያስገድዳቸው ማንንም ሳያስቸግሩ ሁሉም በተሰጣቸው ዕውቀት ፣ በየሠፈሩበት አብያተ ክርስቲያናትን ከሠሩ በኋላ በ፲፱፻፸፬ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ከቦታው ድረስ መጥተው





www.ethiopianorthodox.org

የተሠሩትን አብያተ ክርስቲያናት አንድ ባንድ እየተዘዋወሩ ከጎበኙዋቸው በኋላ ለያንዳንዳቸው ስምን ሰይመው የሚደበሩትንም ደብረው ባርከዋቸውና ጽላት አስገብተውላቸው መመለሳቸው ሳናስታውሰው አናልፍም ከዚያን ጊዜ ጀምረው በመገልገል ይገኛሉ ።

ትንሣኤ ፦ ለመሆኑ እነዚህ ፲፭ አብያተ ክርስቲያናት ብቁ አገልጋዮች ይኖርዋቸዋል ።?

መልስ ፦ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የተሟሉ አገልጋዮች ቀዳሾችና ወዳሾች አሏቸው ምክንያቱም ወደ ሰፈራ የመጡት ሁሉ ማይሞች ብቻ ሳይሆኑ ቀሳውስትና ዲያቆናትም ናቸውና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ችግር የለም ሁሉም ዓቅማቸው በሚፈቅድላቸው መጠን ያገለግላሉ ።

ትንሣኤ ፡ የአሶሳ አውራጃ እንደሚታወቀው ሰፈ መሬት የበሬ ኮቴ የማረሻም ልሳን ያልደረሰበት እንደሆነ ግልጥ ነው ስለዚህ በዚሁ ድንግል ቦታ የሚንቀሳቀስ ልማት እንዳለ ቢያስረዱን ?

መልስ ፦ በእነዚህ ፲፭ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙት ምእመናን ትልቅ ትንሽ ሳይባል ሁሉም ባንድነት መሬቱን እያለሙ ናቸው ። እኔም የ፲፭ቱ አብያተ ክርስቲያናት አስተባባሪእንደመሆኔ መጠን ሁሉም ባንድነት እያራሱና እየቆፈሩ አስደሳች ውጤት እያስገኙ ናቸው ከተመረቱትም በመጠኑ ከዚህ ላይ ብንገልጽ መልካም ይመስለኛል ።

ከእህል ዘር
ከተመረቱት ምርቶች

በቆሎ ፪፻ ፶፬ ኩንታል
ማሽላ ፳፱ ኩንታል
ጤፍ ዜሮ ፯ ኩንታል
ስንዴ ዜሮ ፱ ኩንታል
በርበሬ ፲፫ ኩንታል
ኑግ ዜሮ ፱ ኩንታል
በሎቄ ፳፰ ኩንታል

ተገኝቷል በጠቅላላ ከእህል ዘር የተገኘው ውጤት ፫፻፳፬ መሆኑ ነው ።

# አትክልትና ፍራፍሬ

ማንጎ ፫ሺህ፩፪፰፫ እግር ተክሎ ፍሬውን በመጠባበቅ ላይ ነን ጌሾ ፳ እግር ተክሎ ቀጥሎ ይገኛል ።

እንደዚሁም የሻማ ሥራ በ፩ አብያተ ክርስቲያናት ተጀምሮ ሥራው በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ከመሆኑም ሌላ በባበሲ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤልም ቤተ ክርስቲያን ፫ ክፍል ያለው የዳቦ መጋገሪያ ፩ ክፍል ያለው ዕቃ ቤት ሲኖር ።

እንደዚሁም ለእንግዳ ማረፊያ ፲ ክፍል ያለው ትልቅ ቤት በመሥራት ላይ ይገኛል ።

ትንሣኤ ፦ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ካህናት እንዳሉ ገልጸውልን ነበር ነገር ግን ለካህናቱ የሚከፈል ገንዘብ አለ ወይስ በነፃ ነው የሚያገለግሉ?

መልስ ፦ ተገልጋዮቹ ምእመናን ከሚያገኙት ሁሉ እንደየዓቅማቸው ይሰጥዋቸዋል ። ከምእመናን የሚያገኙትን ገቢ እየተቀበሉ ነው የሚያገለግሉ የሚሰጥዋቸውም ከእህል ነው እንጂ ጥሬ ገንዘብ አይደለም ።

ትንሣኤ ፦ ሌላስ ያለማችሁት እንዳለ ቢያብራሩልን ?

መልስ ፦ በሌላ በኩል ከማንጎ ከጌሾ ሌላ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ቅጥር ግቢ የተለያዩ ዛፎችን በመትከል ላይ ነን ከምንተክላቸውም ዛፎች መካከል ።

ጥድ ፣ ዝግባ ፣ አርዘ ሊባኖስ ፣ ባሕር ዛፍ የመሳሰሉት ናቸው ፣ ከዚህም ሌላ አብያተ ክርስቲያናቱ ከዚህ ቀደም ሣር ለብሰው ይኖሩ ነበር ዛሬ ግን ቆርቆሮ እየለበሱ ናቸው ። እንዲያውም ከ፲፭ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አንድ ብቻ ቆርቆሮ ሳይለብስ ሲቀር ፲፬ቱ ሁሉ በሚያስደስት ሁኔታ ቆርቆሮ ለብሰው ይገኛሉ ።

ትንሣኤ ፦ ከልማት ብዙ እህል እንደተገኘ ተገልጿል ነገር ግን ከልማቱ የተገኘው ገቢ ከምንድን ነው የሚውለው ?

መልስ፦ ከልማቱ የሚገኘው ገቢ ለአንዳንድ ንዋየተ ቅድሳት ማሟያና ለፈረሰ መጠገኛ ሊሆን ከዚያ የቀረ ደግሞ ለካህናቱ መደጐሚያ ይሆናል በማለት መልአከ ኃይል እንየው ውቤ ገልጸውልናል ።

መልአከ ኃይል እንየው ውቤ በሠሩት ሥራና ባስገኙትም የሥራ ውጤት ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ፊት ቀርበው ሙሉ ልብስ ተሸልመዋል ይኸውም ይደልዎ አስቡ ለዘይት ቀነይ ለሠራተኛ ዋጋው ይገባዋል ተብሎ የተጻፈው መሠረት መልካም ሥራ ሠርተው ስለተገኙ ነው ።

ስለዚህ እኛም መሬቱን በማልማት ራሳችንን እንድንረዳ ያስፈልጋል ።
ክነፈ ርግብ ማርቆስ



ዝናም ለዘር ጠል ለመከር አስፈላጊ መሆኑ ለማንም የተሠወረ ሳይሆን በጣም ግልጽ የሆነ ነው እንግዲህ ስለዝናም አስፈላጊነትና ለዘር ፣ ተስማሚነትና ጠቃሚነት ከተነሳን የሚከተሉትን ሥጋውያንና መንፈሳውያን ተግባሮች መመልከቱ እጅግ በጣም ጥሩ ነው ።

ገበሬው በበጋው ወራት መሬቱን አርሶ አለስልሶና አሳምሮ ፣ አበጃጅቶ የሚቆረጠውንም ቁጥቋጦ ቆርጦ የደረቀውን ሣርና ጉልጓሎውን ሁሉ ከአንድ ላይ ሰብስቦ በእርሻው መካከል በእሳት ያቃጥለዋል ።

ከዚህ በኋላ እንደገና በድጋሚ እርሻውን ያርስና ቅብቅቡን አስቀድሞ ደመናው ሲዘር ሰማዩ ሲያስገመግም የክረምቱ ወራት ሲቃረብ ያ ትጉሑ ገበሬ ለመሬቱ ተስማሚና ተመጣጣኝ የሆነውን የእህል ዘር መርጦ በተገቢው እርሻ ይዘራዋል ።

ዝናሙም ሲዘንምበት ያ በመልካም መሬት የተዘራው ዘር ያማረና የሰውን ዐይን የሚማርክ ቡቃያ ሁኖ ይበቅላል

ከዚያም ቡቃያውን ማንም እንዳይረግጠውና ከብቶችም እንዳይበሉት አጥር አጥሮ በእንክብካቤ ይጠብቀዋል ኋላም አብቦና አፍርቶ ጉምርቶ የመከሩ ወራት በደረሰ ጊዜ እንኳንስ የዘራው ገበሬ ይቅርና ተመልካቹ ሁሉ በደስታ ይረካል፣ ምርቱም በዓውድማው ላይ ይትረፈረፋል ከቤተሰብም አልፎ ለጎብረ ተሰቡ በገበያ ላይ ለሽያጭ ይቀርባል መሬቱ ሳይዘጋጅ የተዘራ ዘር ግን ቢበቅልም ሊጠቅም አይችልም ።

ከዚህ ላይ ይህ ጥሩ ምርት የሚገኘው በብዙ ጥረትና ድካም መሆኑ መዘንጋት የለበትም ፣ ይኸውም የመጀመሪያው ሰው ከፈጣሪው የተሰጠው ትእዛዝ በኦሪት ዘፍ ም ፫ ቁ. ፳-፱ "በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም የምድርን ቡቃያ ትበላለህ ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ " የሚል ነበር ይህ አምላካዊ ቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ እስከ አሁን ድረስ ማንኛውም የሰው ዘር በሙሉ እስከ መጨረሻው ኅል

# ዝናም ለዘር

ፊት ድረስ ሲጠቀምበት ይኖራል ።

ሌላውም ሕይወት ያለው ተንቀሳቃሽ እንስሳም ቢሆን ለሚመገበው ዕለታዊ ምግቡ ደክሞ ወጥቶ ወርዶ ማግኘት እንዳለበት በተጨማሪ ያስተምራል ይህን በመደገፍ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር ፩፻፳፭ ቁ ፭ ላይ "በለቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ" ሲል የተናገረው ቃል ሰው ደክሞ ፣ ጥሮ ግሮ ኑሮውን ለማሻሻልና የድካሙን ዋጋ እንደሚያገኝ ጉልህ አድርጎታል ብንል ከእውነት አልራቅንም ምክንያቱም ሰው ካልሠራ አይበላምና ነው ጠቢቡ ሰሎሞንም በመጽሐፈ መክብብም ፲፩ቁ፯ ላይ ስለ ሰው ልጆች በሥራ ብልጽግናን ለመግለጽ ምክርና ትምህርት ሲሰጥ "የእግዚአብሔርን ሥራ አታውቅም ወይም ይህ ወይም ያ ማናቸውም እንዲበቅል አታውቅም ወይም ሁለቱም መልካም እንዲሆኑ አታውቅምና በማለዳ ዘርህን ዝራ " ።

በማለት የተናገረው የማበረታቻ ቃል በወቅቱ ሥራችንን ሠርተን እንድንፈጽምና ጊዜያችንን በከንቱ እንዳናባክን የዘሩ ወራት ዛሬ ወይም ነገ ሲባል እንዳያልፍ ማስጠንቀቂያ ከመሆኑም በላይ አንዳንድ ሰነፎች ስለማይጠፉ እነርሱንም ለመገሠጽ ነው ይኸውም በአገራችን የአነጋገር ዘይቤ "ለሞኝ ሰኔ በጋ ው ነው " ይባላል ይህ አባባል የሚያስረዳን ከላይ በርእሱ የተገለጸው ዝናም ለዘር አስፈላጊው መሆኑን ነው ስለዚህ እንዲሁ ተቀምጠን ጊዜን ለማሳለፍ የዝናሙ ወራት ሲቃረብ "ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ" እንዳይሆን ሁሉም በጊዜያቱ መሠራት እንዳለበት ያመለክታል ።

ይሁን እንጂ ሥጋዊ ሥራ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ሥራም በጊዜው መከናወን እንዳለበት ማለትም ዕለተ ሞትን ስለማናውቅ ባለንበት የእድሜ ዘመን መልካም ሥራ ሠርተን እንድንጠቀም ያስገነዝበናል ይህ ብቻ አይደለም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል ም ፰ ቁ. ፭ " ዘሪ ዘሩን ሊዘራ ወጣ ሲዘራም አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ ተረገጠም የሰማይ ወፎችም በሉት ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ እሾሁም አብሮ በቀለና አነቀው ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀ በበቀለም ሊዜ መቶ እጥፍ አፈራ" እያለ በምሳሌ ግልጽ አድርጎ ቅዱስ ቃሉ ያስተምረናል ። ይህ ትምህርት በሰምና ወቅር መልክ የቀረበ ሲሆን ትርጓሜውን ከቅዱስ መጽሐፍ ተመልክቶ መረዳቱ ለአንባቢያን አያዳግትም ነገር ግን ሁልጊዜ በአዕምሮችን ውስጥ ትኩረት ልንሰጥበት የሚገባን አንድ ዓቢይ ጉዳይ አለ ።

ይኸውም ዘሪው ወይም ገበሬውን ማን ነው ? ክርስቶስ ነው ዘሩስ ከየት ተገኘ ? ዘሩም የእግዚአብሔር ቃል ነው እርሻውስ ? እርሻውም የእኛ እዝነ ልቡና ነው ታድያ ይህ ከሆነ እስቲ እዝነ ልቡናችነን እንመርምር እንደ መልካሙ መሬት የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ለመቀበልና ተቀብሎም ከስራ ላይ ለማዋል ተዘጋጅቷል ? ወይስ በጎ ለት ላይ እንደ ወደቀው ዘር ልቡናችን ዓለት በመሆን ቅዱስ ቃሉን ለመቀበል ካለመቻሉ የተነሳ ባዶ ዓለት እንደሆነ ይገኛል ? ወይስ ደግሞ በእሾህ መካከል እንዳበቀለው ዘር ለማደግና ለማፍራት እንዳልቻለው ሁሉ ልቡናችን በቂም በቀል ታንቆ ወደ ክርስቶስ ለመመለስ ሳይችል እንደቀረ ነው ? ወይስ ተመልሷል? ።

ከዚህ ላይ የምንከተለው ፍሬ ነገር ቢኖር ዓለቱንና የሾሁን ምድር ሳይሆን ሕሊናችንን መልካም መሬት አድርገን አለስልሰንና አሳምረን በስነ ምግባር በሃይማኖት ጸንተን የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብለን ወደ ግራም ወደ ቀኝም ሳንል በቀጥታ ቅዱስ ቃሉን ጠብቀን መገኘት እንዳለብን ነው ።

ከላይ የሰማይ ወፎች የተባሉትም ጠላቶቻችን አጋንንት ስለሆኑ በእኛ ላይ የተዘራውን ቅዱስ ቃሉን ከእኛ ላይ እንዳይለቅሙ የምንከላከልበት ድል የምንነሣባቸው ምግባርና ሃይማኖት ናቸውና ምግባራችንና ሃይማኖታችን አጽንተን ለመኖር ያብቃን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ዕረፍት

የመልአከ ገነት ሞገስ ዕቁብ ጊዮርጊስ አጭር የሕይወት ታሪክ መልአከ ገነት ሞገስ ከአባታቸው ከአቶ ዕቁበ ጊዮርጊስ ወልደ ኢየሱስ ከእናታቸው ከወ/ሮ ወለተ ትንሣኤ ኃይለ ሚካኤል በኤርትራ ክፍለ ሀገር በሐማሴን አውራጃ በለጎጭዋ ወረዳ ልዩ ስሙ ክትሞውሊዕ በተባለው መንደር መስከረም አንድ ቀን ፲፱፻፳ ዓ/ም ተወለዱ በተወለዱ በ፲፪ ዓመታቸው በትምህርት ተኮትኩተው እንዲያድጉላቸው ወላጆቻቸው እምኒ ጸሊም ከነበሩትና የኔታ እንድርያስ ዓሰቡ ወደ ተባሉ መምህር ላኳቸው ከዚያ ፊደልን ቆጥረው ቃል ትምህርትንና ቁም ጽፈትን ተማሩ ከዚያም ወደ ትግራይ ክፍለ ሀገር እንድርታ አውራጃ ደብረ ኃይላ በሚል ስም ወደታሐወቀችው ገዳም ገብተው ስመ ጥር ከሆኑ ከመምህር ገብረ ሕይወት ጎምሎቅኔ ከነ አገባቡ ተምረው ለመምህርነት ተመርቀዋል ።



መ. ገነት ሞገስ እኒህ ነበሩ

መ/ገነት ሞገስ ከዚያ ሳይወጡ አየይዘው ከዚሁ ቦታ ከየኔታ ፈለቀ አቋቋምን በሚገባ ተማሩ ከዚህ በኋላ ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር በመሻገር በደብረ ታቦር አውራጃና በዚሁ አካባቢ የጎንደርን አቋቋም የጸናጽሉን አወራረድንና ይትበሃሉን ለመለየት በጎንደር አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወሩ ይትበሃሉን ካጠናቀቁ በኋላ የትምህርት ፍላጎታቸው ስላልተሟላላቸው እንደ ገና የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለመማር በ፲፱፻፳፯ ዓ/ም ወደ ሸዋ ክፍለ ሀገር አዲስ አበባ ሄደው ከዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ት/ቤት (በዓታ) ገብተው ከአለቃ ኅሩይ መጻሕፍተ ሊቃውንት አቡሻህርን (ባሕረ ሐሳብ) ከመማራቸውም በላይ ከታወቁት ከዶክተር አለቃ አየለ ዓለሙ ደግሞ የ፹፩ መጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ በሚገባ ትምረዋል ።

መልአከ ገነት ሞገስ በመምህሮቻቸው ዘንድ የተመሰለኑና በሚያሳዩትም ትጋት ተደናቂነትን አትርፎላቸዋል ።

መልአከ ገነት ሞገስ ከበዓታ ወደ ቅዱስ ማርቆስ ከማርቆስም ወደ በዓታ እየተመላለሱ ትምህርታቸውን በመልካም ይዞታ ሲያካሄዱ ሳሉ በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ኃይለኛ የጠላት ጦርነት ስለ ተጀመረ በዚህ ጊዜ ትምህርታቸውን አቋርጠው ፱ ቀንና ፱ ሌሊት በመታሠር እህለውኃ ሳይቀምሱ ልዩ ልዩ ሥቃይን በመቀበል ከሰነበቱ በኋላ ወደየክፍለ ሀገራችሁ ግቡ ስለ ተባለ ከታሠሩት ተፈትተው የትምህርት ሞያቸውን ይዘው ወደ ኤርትራ ክፍለ ሀገር ተመለሱ ከዚያም በሕፃንነታቸው ፊደል ከቆጠሩበት ቦታ ለጥቂት ቀን ሲያስተምሩ ከሰነበቱ በኋላ ወደ ደብረ ድማኅ ገዳም ገቡ (የአቡነ መርቆሬዎስ ገዳም ነው ።)

ከገዳሙም ገብተው የተማሩትን ሞያ እያስተማሩ ብዙዎችን ደቀ መዛሙርት ከማፍራታቸውም በላይ የተማረኩት ይበቃኛል ሳይሉ ከገዳሙ አበምኔት ከመምህር ገ/እግዚአብሔር ቅዳሴን ተምረዋል ።

መልአከ ገነት ሞገስ ከገዳሙ ወጥተውም በስንሒት አውራጃ በከረን ከተማ በልደታ ማርያም ቤተክርስቲያን ወምበር ዘርግተው ጉባኤያትውን አስፋፍተው ቅኔንና ቅዳሴን እንዲሁም መጻሕፍተ ሐዲሳትን በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ።

መ/ገነት ሞገስ ሰውን ሁሉ ትልቁን ትንሹን በሚዛናዊ ዓይን ይመለከቱ ነበር እንጂ ሰውን ከሰው አበላልጠው አይመለከቱም ነበር በዚህም ምክንያት የሰላም አባት የሚል ቅጽል በስማቸው ላይ ተቀጽሎላቸው ነበር ።

ለሀገር ያበረከቱት አገልግሎት

መ/ገነት ሞገስ ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖትን ከመሠረቱት አባሎች አንዱ ሲሆኑ በዚሁ ድርጅት በዋና ፀሐፊነት በምክትል ሊቀ መንበርነት በመሥራታቸው ቀዋሚና ለሁልጊዜ በማይናወጽ መዋቅር ስላዋቀሩት እነሆ ማኅበሩ በማይናወጽ ዓለት ተመሥርቶ በየጊዜው መንፈሳዊ ፍሬውን እያበረከተ ይገኛል ።

መንፈሳዊ ስነጽሑፍ

በመንፈሳዊ ሥነ ጽሑፍም ቢሆን በኮከበ ጽባሕ እየታተሙ የሚወጡ ቅዱሳት መጻሕፍት ሆኑ ብሎያትና መጻሕፍተ ሐዲሳት ሌሎች የጸሎት መጻሕፍትም ሁሉ ምሥጢራቸው እንዳይፋለስ ዘራቸው እንዲይዘባረቅ በጥንቃቄ የሚያርሟቸውና የሚያስተካክሏቸው እሳቸው ነበሩ እነዚህ መጻሕፍት ታርመውና ታትመው ለምእመናን የሚደርሱ በእሳቸው ድካምና የሥራ መሥዋዕትነት መሆኑ ሥውር አይደለም ።

መ/ገነት ሞገስ በተማሩት መንፈሳዊ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተጠይቀው በሚሰጡትም አጥጋቢ መልስ በሕዝቡ የነበራቸው ተወዳጅነት ወሰን አልነበረውም መ/ገነት ሞገስ በትምህርት ካገኙት ዕውቀት ሌላ ከእግዚአብሔር በጸጋ የተሰጣቸውም የተፈጥሮ ዕውቀትና ጥበብ ተመሳሳይ አልነበረውም

ትምህርተ ወንጌል

በልዩ ልዩ ቦታዎች ሕዝብ በሚሰበሰብበትና በየአብያተ ክርስቲያናቱ መድረክም ተገኝተው ቁመው በሚያስተምሩበት ወቅት ጣዕመ ስብከታቸው የደረቀውን የሚያርስ የጠወለገውን የሚያለመልም ስለ ነበር ሕዝቡ ሁሉ ትምህርታቸውን ለመስማት አፉን ከፍቶ ጆሮውን አቀርቅሮ የሚያደምጣቸው ምን ያህል የትምህርት ርካታ እንደሚያገኝ ሕዝቡ ራሱ ምስክር ስለሆነ ለሕዝቡ እንተዋለን ።

መ/ገነት ሞገስ ካህናትና ምእመናን የሚጠቀሙባቸው በግዕዝና በአማራኛ አዘጋጅተው እያሳተሙ ለምእመናን ያቀረቧቸውና በሕዝበ ክርስቲያን እጅ የዋሉ መጻሕፍት በክፈል የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ መክሰተ ልሳን ዘሕፃናት
፪ኛ/ አንጋፋ ፈላስፋ በአማርኛ
3ኛ/ ሰዓታት ዘምስለ ባሕረ ሐሳብ
፬ኛ/ ሥነ ፍጥረትና አዕማደ ምሥጢር
፭ኛ/ መጽበል አምኃ ሰላም
፮ኛ/ ጥንታዊ ምሳሌ በትግሪኛ
፯ኛ/ ጥንታዊ ምሳሌ በአማርኛ
፰ኛ/ መዝገበ ቃላት በአማርኛ
፱ኛ/ መርሐ ጽድቅ ባሕለ ሃይማኖት በአማርኛ

የተሰኙትን መጻሕፍት በኢትዮጵያ ተዘርግተው በምእመናን እጅ ውለው ጽምዓ ትምህርትን አስወግደው ሲገኙ ሌሎችም እትመትን የሚጠባበቁ ከላይ የተጠቀሱትን ያህል እንዳሉ ካሳተሟቸው መጽሐፍት ተገልጸዋል ።

ከዚህም ሌላ ዜና ሐዋርያትና ፍኖተ ብርሃን በቸባሉት መንፈሳውያን ጋዜጦች ምን ያህል ትምህርት ያስተላልፉ እንደነበር በጋዜጦቹ የሠፈረው ጽሑፍ ምስክር ነው ይህ ብቻ አይደለም በዘመናዊ ስነ ጽሑፍም ከዘመኑ ትውልድ ጋር የሚስማማ ሳይንስ ነክ የሆኑትን የፍልስፍናና የሀገርን ባሕል የሚያንጸባርቅ ብዙ መጻሕፍት አበርክተዋል ለምሳሌ መዝገበ ቃላት አማርኛ በአማርኛ የሚለው አንጋረ ፈላስፋ የተባለው ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉት መጻሕፍት የመ/ገነት ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ውጤቶች ናቸው እነዚህን መጻሕፍትና በብዙ ድካም አሳትመው ለሕዝብ የቀረቧቸው የፍልስፍና መጻሕፍት የሚሰጡት ጥበብ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

መ/ገነት የደረስዋቸው መጻሕፍት ጣዕም ያላቸው ናቸው ። ሁሉ ይሰለቻል የእሳቸው ድርሰቶች ግን ሲያነቧቸው ልቀቁኝ የሚሉ አይደሉም ። የየዛቸውን ሰውወበግድ ይዘው እንዲያነባቸው የሚያስገድዱ ናቸው ።

የመ/ገነት የፍልስፍና አነጋገር ፡

መ/ገነት ካሳተሙት መጽሐፍ ሥዕላቸው አለ ታድያ ከሥዕላቸው ሥር ያለው አነጋገር አስደናቂ ነው ።

ይህ ሞገስ ነው ትሉኝ ይሆናል ግን እኔ ምሳሌው (ስዕሉ) እንጂ ሞገስ አይደለሁም ሞገስ አንድ ነው እኔ የሞገስ ስዕል ግን አንድም ብዙም ነኝ ።

ሞገስ ከአንድ ቦታና ከአንድ ቤት ይገኛል እኔ ግን ከብዙ ቦታና ከብዙቤት እገኛለሁ ሞገስ ዛሬ አለ ነገ ግን እንጃ ከነገ ወድያ ግን በእርግጥ የለም እኔ ስዕል ግን ዓለም እስካለ ድረስ ከእናንተ ካሕያዋን ጋር አለሁ ።

ይሁን እንጂ እሱ ሲታመም የማይታመም እሱ ሲሞት የማይሞት አንድ ነገር በአደራ ሰጥቶኛል ይኸውም በ፫ ቀለሞች የቆመ ስም ነው እስካሁን ድረስ ከእኔ አልለየውም በማለት የተናገሩት ዓቢይ ቃል የፍልስፍናቸው ማንጸባረቂያና እኛንም የሚያሳስብና የሚያስገነዝብ ነው ።

ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጰስዮስ በጻፈው መልእክቱ (እፈቱስ እፍልስ ወእትፈለጥ እምዝንቱ ዓለም ከመ አሃሉ ኅበ ክርስቶስ) "እኔ ከክርስቶስ ጋር እኖር ዘንድ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቼ ለመሄድ እናፈቃለሁ" ፊል ፩፣ ፳፫ ሲል እንደተናገረ ሁሉ መ/ገነት ሞገስም ሞትን ይናፍቁት ነበር እንጂ ሞትን አይፈሩም ነበር።

ይኸውም ገና በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ሞታቸውን ሲያረጋግጡ ራሳቸው እኔ ዛሬ አለሁ ከነገ ወድያ ግን የለሁም ማለታቸው ዕፁብ ድንቅ ነው ።

እንግዲህ ዛሬ አለሁ ነገር ግን የለሁም ብለው እንደ ተናገሩም ትናንት ከእኛ ጋር ነበሩ ዛሬ ግን ከእኛ የሉም ይሁን እንጂ ዛሬም ቢሆን ከእኛ ጋር የሉም ለማለት አንችልም ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ምንም እንኳ በሥጋዬ ከእናንተ ባልኖርም በመንፈሴ ከእናንተ ጋር ነኝ ሲል እንደተናገረ ፩ኛ ቆሮ ፭፣፱ ።

መ/ገነት ሞገስም በሥጋቸው ከእኛ ቢለዩም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከእኛ ጋር መሆናቸውን አንዘነጋም ።

አሁንም መልአከ ገነት ሞገስ ሆይ ያ ከሕፃንነት እስከ ሽምግልና ድረስ ያገለገሉት አምላክ ያችን የማታልፈውን ሰማያዊት ርስት ያውርስዎት ዘንድ በጸሎት እናስታውስዎታለን ።

ከማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት የስብከትና የድርሰት ክፍል አሥመራ

# ሰው በአግባቡ ቢሠራበት ሕግ መልካም ነው

ማንኛውም ፍጥረት የተሠጠው የራሱ የሆነ ሕግ አለው የተሠጠውንም ህግ ሳያጓድል በሕግ ተፈጥሮ ሲመላለስ ይኖራል ። ለምሳሌ ፀሐይ ጧት ወጥታ ማታ ስትገባ ፣ ሲመሽ ሲነጋ ዕለታት አልፈው ሌሎች ዕለታት ሲተኩ ፣ ሣምንታት በወራት ፣ ወራት ደግሞ በወቅቶች ሲፈራረቁ ፣ ወቅቶችም በዓመታት ሲለወጡ እናያለን ።

በእንስሳትም በኩል በደመ ነፍሀ የሚንቀሳቀሱት ሣይቀሩ በሕገ ባህርይ አውቀው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ፡ መዋለድ ቀስ በቀስ በየጥቂቱ ማደግ መራብ ፣ መጠማት ፣ ምግብ መሻት ይህንኑም ለማግኘት ከቦታ ወደቦታ መንቀሳቀስና የፍሊጋ ጥረት ማሳየት ሲሆኑ ይህን ሁሉ ለማድረግ በተፈጥሮ ጠባይ ሲታዘዙና ሲመላለሱ እንመለከታለን ። ይሁን እንጂ የሚፈርድና የሚያስፈርድ ሕግ እንዳልተሠራላቸው ለዚህም ዕድል ያልተመረጡ ለወቀሳ እና ከሠሣ የማይቀርቡ ለአንክሮና ለተዘክሮ ፣ ለምግበ ነፍስም የተፈጠሩ ለሰው ልጅ ጸጋዎች ሁነው የተሠጡ የሰው ሕይወት አለኝታዎች መሆናቸውን እንረዳለን ።

ስለ እንስሳት ተፈጥሮ ማተቱን ከዚ






www.ethiopianorthodox.org

ሀ እንግታውና በተገቢው መንገድ ቢሰራበት ሕግ መልካም ነው ወደሚለው እንመለስ ከላይ ከተመለከትናቸው ፍጥረታት ሁሉ የበላይ የሆነውን ፍጥረትንም በሀብትነት የመጠቀም መብት የተሰጠው የሰው ልጅ ሀብቱንና ንብረቱን የሚጠብቅበት እንዲ የሌላውን ንብረት ማለትም ኃይለኛው ደካማውን እንዳይቀማው ታታሪው ወጥቶ ወርዶ ያፈራውን ሰነፉ ከጥላ ሥር ተኝቶውሎ ሲፈልግ እንዳይዘርፈው በንብረቱ ምክንያት ውድ ነፍሱን እንዳያጠፋ በሰዎች መካከል ጠብና ክርክር እንዳይነሳና እርስ በእርስ ተለያይተው ከፈጣሪያቸውም አንድነት እንዳይለዩ ፤ በጠቅላላ አነጋገር ለሰው ልጅ የሕይወት መመሪያ ይሆን ዘንድ ከፈጣሪው የተሠጠው ትእዛዝ ሕግ ይባላል ።

አለቃ ኪዳነ ወልድ በሠጡት ትርጓሜ "ሕግ በቋሙ የተወሰነ የተጻፈ ሥርዓት ፤ እውነተኛ ፍርድን የአገር ልማድ ለማድረግ የሚያዝዝ ከማድረግ የሚከለክል አድርግ ወይም አታድርግ የሚል ሲሆን ከነዚህ አድርግ የሚለው ትእዛዝ ሁኖ አታድርግ የሚለው ግን ሕግ ነው" ብለዋል ።

ይህም የትርጉም አሠጣጥ ከራሣቸው አእምሮ ብቻ አመንጭተው የተናገሩት ልብ ወለድ ሣይሆን መጻሕፍትን ገለባብጠው ከመሠረት እስከ ቅርንጫፋቸው መርምረው ያገኙትን መሠረት በማድረግ ለመሆኑ መጻሕፍት ያስረዳሉ " (ኦ.ዘጸ. ፳፬ ፤ ፲፪ ሰሌዳተ ዕብን ዘሕግ ወዘ ትእዛዝ) ሕግና ትእዛዝን ታስተምር ዘንድ የጻፍኩባቸውን የድንጋይ ሰሌዳዎች እሠጥሃለሁ ተብሎ ለሙሴ ጥሪ እንደደረሰውና እንደተሠጡትም ከመጽሐፍት እንረዳለን ።

ስለ ሕግ አመጣጥ መለስ ብለን ታሪክን ከመረመርን ዘንድ እግዚአብሔር ዓለምን አዘጋጅቶ ሰውን ከፈጠረ በኋላ ያለ ሕግ የተወበት ጊዜ አልነበረም የሰው ሁሉ ምንጭ ለሆነው ለአዳም ቃል በቃል ይህንን ብላ ይህንን ግን አትብላ፣ ብሎ ካዘዘበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ሙሴ ድረስ የነበሩትን በሕገ ልቡና ፤ ከሙሴ እስከ ዮሐንስ ትምህርት በሕገ ኦሪት ሲያዝዝና ሲመራ ቆይቶ የሁሉም ፍጻሜ የምትሆን የማትጐረብጥና የማትሻክር፣ ሸክሟ ቀላል ቀንበሯም ልዝብ የሆነች ሕገ ወንጌልን በአንድ ልጁ መሠረተልን ።

ታዲያ በወንጌል ቃል ተመክረን ቃሉን የምንፈጽምና በሕጉ የምንመራ የጽድቅ ፍሬ ባለቤቶች ለመሆን ከመቻልም አልፈን ለምንኖርበት ኅብረተሰብም ምቹና ተወዳጅነትን የምናተርፍ እንሆናለን ። ብንመክር ምክራችን ብናስተምር ትምህርታችን ተቀባይነት ያገኛል ታማኞችና አስታራቂዎች የሰላም መሠረቶች ለመሆን እንበቃለን ።

በሀገርም ደረጃ የመልካም ስነ ምግባር ምንጮች በመሆን ደስተኛ ቤተሰብ እውነተኛና ታማኝ የሀገር አለኝታ የሚሆን ታላቅና የተከበረ ትውልድ ማበርከት እንችላለን ። ይህ ዕድል በሕግ ጥላ ሥር ተጠልለው በሕግ የበላይነት አምነው ለሚኖሩ የታደለ ጸጋ ነውና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሚገባ ለሚሠራበት ሕግ መልካም እንደሆነ ሲናገር "ኦሪትስ ሕጉን ለሚፈጽመው በሕጉ ጸንቶ ለሚኖር ደግ ሕግ ነው " ብሏል ሮ.ሜ. ፯-፲፪ ።

በመሠረቱ ሕግ ለሰው ልጅ ሲሠጥ ለሕይወትም ሆነ ሞት ታላቅ ምክንያት እንደሆነ በጉልህ እንረዳለን ። ውብና ለምለም የሆነችውን ዓለምን አስቀድሞ ከፈጠረ በኋላ አዘጋጅቶና አሣምሮ በመልኩና በምሳሌው እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረው ፈጥሮም ከባህር በታች በዕመቀእመቃት ፤ ከጠፈር በላይ በአየር እየራት ባለው ፍጥረቱ ሁሉ ገዥ አድርጎ አሠለጠነው ዘፍ.፩.፳፮-፴፩

ሆኖም ይህ ሁሉ መብት ሲሠጠው ያለገደብ አልነበረም ። ሊጠብቀው ወይም ከማድረግ እንዲቆጠብም ግዴታ ጭምር ተሠጥቶትም እንደነበር ማስታዎስ ይኖርብናል ። በኦርት ዘፍጥረትም ዕራፍ ፪ ቁጥር ፲፮-፲፯ እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከምታስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሷ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ " የሚለው ኃይለ ቃል ነው ። ቀዳሚ ፍጥረት አዳም ይህን ቃል ጠብቆ መውጣት ካለመቻሉ የተነሣ ከሞት መዘቅት ወድቆ ይማቅቅ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም በመሆኑም የአምላኩን ትእዛዝ ደፍሮ ሕገ እግዚአብሔርን አቃሎ አትብላ የተባለውን ቅጠል በመብላቱ ለ፭ ሺህ ፭፻ ዓመታት በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ ተፈረደበት ።

ሕግ በዚህ መሠረት ያከበሩትን የሚያከብር ፤ የጠበቁትን የሚጠብቅ ሲሆን ለሚዳፈሩት ግን ማረሚያ ፤ ማስጠንቀቂያ ፤ ማስተማሪያ ፤ መገሠጫና መምከሪያም ነው ። ከሕግ ምክርና ተግሣፅ ለማይማሩ የሕግን ሕልውና ፈጽመው ለማይቀበሉና ሕብረተሰብን እንደፈለጉ ለሚያስቸግሩና በግል ኃይላቸው ለሚመኩ ሥርዓት አልባ ግለሰቦች ግን እስከነአካቴውም ሕግ መበቀያ ወይም ማስወገጃ መሆኑን እንረዳለን ።

ምክንያቱም አንድ አመፀኛ በኅብረተሰብ መካከል ካለ የኅብረተሰቡ ሕልውና የተረጋጋና ሰላም የሰፈነበት ሊሆን ስለማይችል ነው ። ኅብረተሰቡን ለማረጋጋትና ፀጥታውን ለመጠበቅ ሲባል ዓመፀኛውን ግለሰብ ማስወገድ ለሚመለከተው ክፍል ግዴታ ይሆናል ። ለዚህም ፍርድ ቤቶች የኅብረተሰብ ነቀርሳ የሆነውን አካል እስከ መጨረሻ ከኅብረተሰቡ አንድ ላይ በፍርድ ይወስኑበታል ።

በትምህርትና በተግሣፅ የማይመለስ በሠራው ስህተት የማይፀፀት አንገተ ደንዳና በመሆኑም በዚህ ዓለም ሥጋ የተወሰነበት ውሳኔ በሌላው ዓለም ነፍስም ይጠብቀዋል እንግዲህ ከዚህ ዓይነቱ የሁለት ዓለም ሞት ለመዳን ፤ በዓለም ሥጋና ዓለመ ነፍስ አስከፊ ፍርድ እንዳይጠብቀን በሰላምና በፍቅር እንኖር ዘንድ ሕግን ያለአድልዎ መማለጃና የሰው ፊት ሣይበግረን በአግባቡ ልንሠራበት ይገባል ። ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ "ለሰው ፊት ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራላችሁ ሕግም እንደተላለፉዎች ይወቅሷችኋል" ሲል ያስተምረናል ። አባ ብርሃነ መስቀል አየሁ



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፥ መንፈሳዊ ዛመናዊ መዝሙሮችን ፥ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ሰባት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቍ.
የመልእክት ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org